ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 342 ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

# መንግሥት ለሰላም መስፈን ያለውን ቁርጠኝነት በየጊዜው እያሳየ መሆኑን አስታወቀ


ፎቶ - ገበበ ገብሬ

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግሥት በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን ችግር ለመፍታትና ለሰላም መስፈን ያለውን ቁርጠኝነት በየጊዜው እያሳየ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አስታወቁ።

ለሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት ዕልባት ለመስጠት የተቋቋመው የሰላም አማራጭ ዐብይ ኮሚቴ ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ ለሆኑ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት ማብራሪያ ትናንት ሲሰጥ፤ የዐብይ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ደመቀ መኮንን እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ሁሌም ቢሆን ለሰላም ቁርጠኛ መሆኑን በተግባር እያሳየ ነው።

መንግሥት የሰላም ንግግር ያለቅድመ ሁኔታ በየትኛውም ቦታ እና ጊዜ ለመጀመር ያለውን ዝግጁነት መግለፁን ያስታወሱት አቶ ደመቀ፤ የፌዴራል መንግሥት የሰላም አማራጭ ቡድን ከማሳወቅ ባለፈ ለተጀመረው አገራዊ የምክክር ሂደት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን

መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# «የዓባይ ግድብ ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ሽግግር የሚበጅ ወሳኝ አቅም ሆኗል»

- ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ
የምጣኔ ሀብት ባለሙያ


ፎቶ - እዮብ ተፈራ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ እያደገ የመጣው የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያ ለምታከናውነው የኢንዱስትሪ ሽግግር የሚበጅ ወሳኝ አቅም ሆኗል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ ተናገሩ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት፤ የዓባይ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ ቱሪዝምን፣ የዓሣ ምርትንና አግሮ ኢንዱስትሪዎችን በማስተሳሰር ረገድ ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዕድገት ትልቅ አቅም ሆኖ ተገኝቷል።

በዓለም ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ አቅም የፈጠሩትን ቻይና፣ አሜሪካ እንዲሁም ሩሲያን ብንመለከት ግዙፍ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦችን ገንብዋል ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ከገነቧቸው ግድቦች የሚያገኙትን ኃይል ለኢንዱስትሪዎችና ለተለያዩ የልማት ሥራዎች በስፋት በመጠቀም የኢኮኖሚ ዕድገታቸውን ማነቃቃት እንደቻሉ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያም ትልቅ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ በመገንባት ለዘርፈ ብዙ ኢንዱስትሪያዊ ጉዳዮች ማዋል የሚቻልበት ዕድል ተፈጥሯል። በዚህ ረገድ ኃይል መስጠት የጀመረው ዓባይ ግድብ የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ሽግግር እንዲቀላጠፍ የሚረዳ ተጨባጭ አቅም ሆኗል ሲሉ አስረድተዋል።

«የዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አቶ ተስፋዬ መገርሳ

# ክልሉ ከማዕድናት ሽያጭ ከ324 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቱን አስታወቀ

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ከማዕድናት ሽያጭ ከ324 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቱ ተገለጸ፡፡

የኦሮሚያ ክልል የማዕድን ልማት ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ መገርሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደገለጹት፣ በክልሉ በርካታ ማዕድናት ቢኖሩም እስካሁን በተደረገው መለስተኛ ጥናት ከተለዩት 48 የተለያዩ ማዕድናት 324 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን ጠቁመዋል፡፡

ሆኖም ያሉትን በርካታ ማዕድናት በጥናት ለመለየትና በተገቢው ሁኔታ ለአገር እድገት ለማዋል ባለሥልጣኑ ሰፊ

ክልሉ ከማዕድናት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## በትግራይ ክልል ለዜጎች የሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ

ገጽ 3

ዜና

# «የኢትዮጵያ ኩራት ለሆነው የዓባይ ግድብ በመሚገቴና የአገሬን ሰንደቅ በማውለብለቤ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል»

**- ሙሐመድ አልአሩሲ**

**በዓባይ ጉዳይ ተሟጋችና የህ/ተ/ምክር ቤት አባል**

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያውያን ኩራት ለሆነው ዓባይ ግድብ ፕሮጀክት በመሚገቴና በዓለም መድረክ የአገሬን ሰንደቅ ማውለብለብ በመቻሌ ደስተኛ ነኝ ሲል በዓባይ ጉዳይ ተሟጋችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሙሐመድ አል-አሩሲ ተናገረ፡፡

ሙሐመድ አል-አሩሲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ ባለፉት ዓመታት በርካታ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ልማትና ብልፅግና ለማፋጠን የሚረዳው የዓባይ ግድብ ለስኬት እንዲበቃ በጋራ ጥረት አድርገዋል።

እኔም እንደ ዜጋ የዚህ ትውልድ አንድ አካል በመሆን በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃኖች ስለግድቡ መከራከር በመቻሌ ደስተኛ ነኝ፤ በዓለም አቀፍ መድረኮችም ስለአገሬ በመሚገቴና ሰንደቋን ማውለብለብ በመቻሌ ኩራት ይሰማኛል ሲል ገልጿል።

እንደ አል አሩሲ ገለጻ፤ የኢትዮጵያን ልማትና ብልፅግና ለማፋጠኛ የሚረዳው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ዩኒት ኃይል ማመንጨት በመጀመሩና የሦስተኛው ዙር ውሃ ሙሌት በተሳካ ሁኔታ በመጠናቀቁ በዓለም አቀፍ መድረክ ስለአገራችን ለምንሟገት ሰዎች ትልቅ የሞራል አቅም ተፈጥሯል።

ባለፉት ዓመታት በግድቡ ግንባታ ዙሪያ ከውስጥና ከውጭ ጫናዎች የበረቱባት ቢሆንም ኢትዮጵያ ፈተናዎቿን እያለፈች አሁን ላይ የዘራችውን ማጨድ ጀምራለች ያለው አል-አሩሲ፤ የዚህች ክንደ ብርቱ ዜጎች አገር አንድ አካል በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፤ በቀጣይም በዓባይ ጉዳይ የበለጠ ለመሥራት ጉልበት አግኝቻለሁ ብሏል።



ከምሥራቅ አፍሪካዊቷ ጥንታዊት አገር ኢትዮጵያ በመሆኔና የ120 ሚሊዮን ሕዝብ ቤተሰብ በመሆኔ ደስታና ኩራቴ የተለየ ነው ያለው አል-አሩሲ፣ «በዓባይ ጉዳይ አገሬ ማንንም ሳትጎዳ ለሕዝቦቿ እና ለዓለም ማኅበረሰብ የገባችውን ቃልም በመጠበቅ በጋራ የመልማት ውጥኗን ማሳካት በመቻሏ ኩራት ይሰማኛል» ሲል ተናግሯል።

እንደ እኔ ዕምነት ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በመልካምነት የልማት ጎዳና እየተጓዘች ትገኛለች ያለው አል-አሩሲ፤ ከልማት ጎዳናዋ ሊያደናቅፏት የሚከጅሉትን ሁሉ መታገል እንደሚያስፈልግ ነው የገለጸው።

ለዚህም ሃሰተኛ መረጃዎችን በመከላከል፣ አጥፊዎችንም በማጋለጥና በተባበረ ክንድ ግንባታውን በማቀላጠፍ ይበልጥ መሥራት እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፏል።

ያሉትን ጫናዎች በፈጣሪ ኃይል፣ አንድነታችንን በማስቀጠልና በዕውነት ላይ በተመሠረተ አሠራር ማሸነፍ ተችሏል ያለው አል-አሩሲ፤ በቀጣይም የመገናኛ ብዙኃን አድማስ በማስፋትና በተለያዩ ቋንቋዎች የሚተላለፉ መረጃዎችን በማጠናቀር በዓባይ ግድብ ዙሪያ የተጀመረውን ስኬት ማስቀጠል እንደሚገባ ገልጿል።

ትውልዱም ከጠላቶች የነሚዙ የሃሰት መረጃዎችን ባገኘው አጋጣሚ በማክሸፍ ሳይሰለች መሥራት ይኖርበታል፤ ከዚህ ባለፈ የአገርና የአካባቢን ሰላም እያስጠበቁ መጓዝ ከተቻለ ከዓባይ ወንዝ የተሻለ ተጠቃሚ መሆን የማንችልነት ምክንያት የለም ሲል ተናግሯል።

ከዚህ ባለፈ የኢትዮጵያውያንን የወደፊት መፃኢ ዕድል የተሻለ ለማድረግ እንዲሁም የቀጣናውን የግልና የቡድን ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ለመቆጣጠር የሳይንስና ፈጠራ ሥራን ከወዲሁ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አሳስቧል።

ለአሁኑና ለቀጣዩ ትውልድ የምመክረው ነገር ቢኖር ወደ ሳይንስና ፈጠራ መንገድ እንዲያዘነብሉና እንዲማሩ ነው። ትውልዱ ወደ ሳይንስና ፈጠራ ማዘንበል ከቻለ ዕውቀትና ክሂሎቱን በማዳበር የተፈጥሮ ሀብታችንን ይበልጥ የምንጠቀምበትን አማራጮች ማስፋት የሚያስችል ዕድል ይፈጠራል ብሏል።

ከሳይስና ፈጠራ ሥራዎች መዳበር ጋር ተያይዞ መቻቻልን፣ ፍቅርንና አንድነትን ማጠናከር ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል።

# ምክርቤቱ መንግሥት እና ሕወሓት በሰላም ውይይቱ ሂደት ላይ በቅን ልቦና እንዲሳተፉ አሳሰበ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት እና ሕወሓት በሰላም ውይይቱ ሂደት ላይ በቅን ልቦና እንዲሳተፉ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት አሳሰበ፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫው እንዳመላከተው፤ መንግሥት እና ሕወሓት በሰላም ውይይት ሂደቱ ላይ በቅን ልቦና እንዲሳተፉ ያሻል፡፡

ጥቅምት 2013 የተቀሰቀሰውን የትጥቅ ግጭት ለመፍታት ከሕዝባዊ ወያነ ሃርነት ትግራይ (ሕወሓት) ጋር የሰላም ድርድር ለመጀመር የኢፌዴሪ መንግሥት አደራዳሪ ኮሚቴ ማቋቋሙን ያበረታታው ምክርቤቱ፤ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ላይ ከፍተኛ ስቃይ ያስከተለውን ይህን ግጭት ለማስቆም የተወሰደውን አወንታዊ እርምጃ እንደሚደግፍም ገልጿል፡፡

ግጭቱ በድርድር እንዲቆም የተስተዋለው ተነሳሽነት ሁሉንም የአገሪቱን ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግ ወሳኝ ውሳኔ ነው ያለው ምክር ቤቱ፤ ይህ ውሳኔ በተደራዳሪ ወገኖች ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተሉ ባሉ በሁሉም ቁልፍ የአገር ውስጥ እና የውጭ አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ እንደሚያምን ነው የገለጸው።

ግጭቱን በሰላም የመፍታት ተነሳሽነት ሙሉ በሙሉ እንደሚደግፍ የገለጸው ምክርቤቱ፤ ጥረቱ የተሳካ እንዲሆን የሰላም ውይይት ሂደቱ ሁሉንም ቁልፍ ባለድርሻ አካላት በተለይም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ያሳተፈ ሊሆን እንደሚገባ በጥብቅ እንደሚያምንም ነው ያመላከተው። ይህም የሰላም ድርድር ሂደቱ ቅቡልነት እንዲኖረው ከማድረግ ባለፈ ውጤቱ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ እንዲችል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋልም ብሏል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሰላም ሂደቱ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና ግምት ውስጥ እንዲገባና በሂደቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ድጋፍ እንዲያደርግ ምክር ቤቱ ጠይቋል።

ECSOC

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የትጥቅ ግጭቱን በሰላማዊ ውይይት ለመፍታት ለሚደረገው የሰላም ማስፈን ሥራ ሙሉ ድጋፉን እንደሚሰጥ የገለጸ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ፍትሃዊና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በሚደረገው ሁሉ ለሰላም ግንባታው ሂደት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ያለውን ጥልቅ ቁርጠኝነት እና ዝግጁነት አሳውቋል።

በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ዘርፉን የመወከል እና የማስተባበር ሕጋዊ ስልጣን የተሰጠው ምክር ቤቱ፤ ለሰላም ያለውን ጠንካራ አቋም በተደጋጋሚ ከማሳወቁም በላይ ሁለቱም ወገኖች ልዩነታቸውን በሰላማዊ ውይይት እንዲፈቱ ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሠረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን በኢፌዴሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግበው ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን በሙሉ በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ3700 በላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።

# በአዲሱ በጀት ዓመት ከወጪ ንግድ አምስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ከወጪ ንግድ አምስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱን የንግድ እና ቀጣናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የንግድ እና ቀጣናዊ ትሥሥር ሚኒስትር ዴኤታ ካሳሁን ጎፌ ሚኒስቴሩ በቅባት እና ጥራጥሬ ዘርፍ ላይ የወጪ ንግድ የ2014 በጀት ዓመት አፈፃፀም እና የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫ ላይ ትናንት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ 2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ከወጪ ንግድ አምስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል፡፡ ዕቅዱን ለማሳካት በተለይም የወጪ ንግዱን 72 በመቶ በሚይዘው የግብርናው ዘርፍ ላኪዎች ትልቅ ኃላፊነት ይጠብቃቸዋል።

MOTRI

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

Ministry Of Trade & Regional Integration

በተያዘው በጀት ዓመት በተለይም የግብርና ምርቶችን ዓይነትና በመጠን በመጨመር የቅባት እና ጥራጥሬ እህሎች ኤክስፖርት ብቻ 595 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መታቀዱን ጠቁመው፤ ይህን ለማሳካትም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት 4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር ከወጪ ንግድ የውጭ ምንዛሬ መገኘቱን አውስተው፣ አፈፃፀሙ አገሪቷ ከነበረችበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የሚበረታታ መሆኑ አውስተዋል።

ባለፉት ዓመታት የወጪ ንግድ አፈፃፀም ዕድገት እያሳየ ሲሆን፤ በቅባትና ጥራጥሬ እህሎች ዘርፍ ግን አሁንም መሻሻል እንዳለበት ተገልጿል።

የቅንጅታዊ አሠራር ጉድለት፣ ቴክኖሎጂ መር አገልግሎት አለመኖር፣ የአማራጭ ገበያ ፕሮሞሽን ሥራ ጉድለት፣ ክትትል እና ቁጥጥር ማነስ፣ ሕገ ወጥነት እና ኮንትሮባንድ የዘርፉ ተግዳሮቶች ነበሩ ተብሏል።

ዓለም አቀፍ ገበያ መቀዛቀዝ፣ የገዥ አገራት መስፈርት ተለዋዋጭነት እና ላኪዎች የገዥ አገራትን መስፈርት ያለማሟላት፣ ያለአግባብ የምርት ክምችት፣ ያልተገባ የአገር ውስጥ ገበያ ፍለጋ እና የምርት ጥራት ማነስ የዘርፉ ችግሮች እንደሆኑም ተወስቷል።

ወደ ውጭ መላክ ያለበት ምርት ከአምራቹ ተሰብስቦ በሦስት ወራት ውስጥ ወደ ውጭ መላክ ቢኖርበትም አሁን ላይ የሚስተዋለው ግን ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት እንደሚከማች ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ እና በዙሪያው ባሉ ከተሞች ፍተሻ ተደርጎ በፍጥነት እንዲላኩ አቅጣጫ ቢሰጥም አሁንም ቢሆን በላኪዎች መጋዘን ያለውን ረጅም ጊዜ የዘለቀ ከፍተኛ የምርት ክምችት ማቃለል እንዳልተቻለ ተናግረዋል።

ምርቱ በወቅቱ ለውጭ ገበያ ባለመቅረቡ ለምርት ጥራት መቀነስና አገሪቷ ማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሬ በወቅቱ እንዳታገኝ ማድረጉን ጠቅሰዋል።

በመሆኑም ላኪዎች ምርታቸውን በወቅቱ ለዓለም ገበያ ማቅረብ እንደሚገባቸው ነው ያሳሰቡት። ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የቅባት እና የጥራጥሬ ምርትን ያለአግባብ አከማችተው በተገኙ ላኪዎች ላይ እርምጃ እንደሚወስድም አስታውቀዋል።

የመድረኩ ተሳታፊ ላኪዎች እንዳሉትም ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች በከፊል ያለቀላቸው ቢሆኑ የውጭ ምንዛሬ መጠን ብቻ ሳይሆን የወጪ ምርቶችን መጠንም ማሳደግ እንደሚቻል ገልጸዋል።

በወጪ ንግድ ዘርፍ እየተካሄዱ ያሉት የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያዎች እንዲፋጠኑ፣ የምርት ዓይነት ስያሜ ጉዳይ፣ በቱሪስት ቪዛ ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ምርቶችን በሚልኩ ደላሎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ ጠይቀዋል።

ለምርት ጥራት መጓደል መንስኤ የሆነው የምርት ክምችት ችግር መቀረፍ እንዳለበት እና ለክምችቱ መንሥኤ የሆኑ ከውጭ ምንዛሬ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዲፈቱ ጠይቀዋል።

በሌላ በኩል ሕገ ወጥነት ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዲወሰድ፣ በጎ የሠሩት ላይ ደግሞ የማበረታቻ እርምጃዎች እንዲረጉ መጠየቃቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ጨምሮ ከሌሎች መንግሥታዊ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ካሳሁን ጎፌ ገልጸዋል።



# የታላቁ ህዳሴ ግድብ ስኬት ለቀጣናዊ ትስስር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የታላቁ ህዳሴ ግድብ ስኬታማ መሆኑ ለቀጣናዊ ትስስር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ የልማት ፕሮጀክት እንደሆነ ያረጋገጠ መሆኑን በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህርና የዓባይ ውሀ ተመራማሪ የሆኑት አቶ አበበ ይርጋ አስታወቁ።

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ መምህርና የዓባይ ውሀ ተመራማሪ የሆኑት አቶ አበበ ይርጋ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ የሁለተኛው ተርባይን ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ባሻገር ደስታና ተስፋን ያጠናከረ ነው። እንዲሁም ጠንካራነትንና ኃያልነትን አብሮ አመንጭቷል ብለዋል።

የጎረቤትና የኢትዮጵያ ወዳጅ አገራት ከኢትዮጵያ ልማት ተጠቃሚዎች ናቸው ያሉት ተመራማሪው፤ ይህ ብስራት ለሁሉም ደስታን ይፈጥራል። በዚህ አመት የተጀመረውን ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ስምምነትን ይበልጥ ከፍ የሚያደርግ ነው። ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ልማት ተጠቃሚ የምትሆንበት ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ፣ ኬንያና ደቡብ ሱዳን የጀመሩት የሦስትዮሽ የመንገድና የባቡር መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ከፍተኛ ኃይል የሚፈልግ በመሆኑ ኢትዮጵያ የበኩሏን ሚና መጫወት እንድትችል ያስችላታል። ከፍ ሲልም ለቀጣናዊ ትስስር ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ መሠረተ ልማት መሆኑን ያረጋገጠ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ተስፋንና ልማት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው። የኢትዮጵያ ልማትና ማደግ የጎረቤትና የወዳጅ አገራት ጭምር ነው። እንዲሁም የተሳሰረ አንድ ዓይነት ዕጣ ፈንታ እንዳለን ያረጋገጠ የልማት ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

ሁለተኛው ተርባይን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ልማታችን ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል ያሉት አቶ አበበ፤ ኢትዮጵያውያን ውስጣዊ ችግሮችን ተቋቁመን ማልማት እንደምንችል ያረጋገጥንበት ነው። ኢትዮጵያ ጠንካራ አገርና የጠንካራ ሕዝቦች ባለቤት በመሆኗ ከራሷ አልፋ ለጎረቤትና ለወዳጅ አገራት በልማት መተሳሰር የሚያስችል የልማት ፕሮጀክት መሆኑን ጠቁመዋል። እንዲሁም በቀጣናው የሚኖሩ አገራት አንድ ዓይነት ዕጣ ፈንታ እንዳለን በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ግድብ መሆኑን ያረጋገጥንበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የልማት ፕሮጀክት በመጀመሯ በጠላት አገራት ጫና ውስጥ የገባችበት ነው ያሉት ተመራማሪው፤ በሴራና ተንኮል ሰለባ የሆነችበት ጭምር ነው። ነገር ግን የሚችሉትን ሁሉ ጫና ቢያደርጉም ኢትዮጵያ የማትበገር አገር መሆኗን በግድቡ ሂደት እያሳየች ነው። ከምንም በላይ ጠንካራና አንድ የሆነ ሕዝብ እንዳላት ያረጋገጠችበት የብስራት ድል ነው። በተለያዩ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች ኢትዮጵያ ጫና ውስጥ የገባችበት አመት ነው፤ የፖለቲካ አለመረጋጋቱ ሕዝቦቿንና አገረ መንግሥቱን የጎዳበት አመት ቢሆንም ይህን በመቋቋም የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ሳይስተጓጎል በጥራትና በፍጥነት በመገንባት የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያመነጭ ማድረግ መቻሉ ትርጉሙ ትልቅ ነው። በተለይ ከዲፕሎማሲ አንጻር ለኢትዮጵያና ለወዳጅ አገራት ትልቅ ድልን ያቀዳጀ ነው ብለዋል።

እንደ መምህሩ ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች ኢትዮጵያን ወደ ኋላ ማስቀረት እንደማይችሉ ያሳየንበትና ትልቅ መልዕክት ያስተላለፍንበት የልማት ፕሮጀክት ነው። ግድቡ እየተገነባ ያለው ለጋራ ተጠቃሚነት መሆኑን እንዲገነዘቡና ጠላቶቻችን አሁን የያዙትን አቋም ቆም ብለው እንዲስቡት ዕድል የሰጠ ነው። ከኢትዮጵያ ጋር መተባበር እንዲችሉ የሚያደርግ ነው። ለኢትዮጵያ በዲፕሎማሲውም ሆነ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል።

# በትግራይ ክልል ለዜጎች የሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ለዜጎች የሚደረገው ድጋፍ አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ከሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ነሐሴ ሦስት ቀን 2014ዓ.ም ድረስ 300 ሚሊዮን ብር ወደ ክልሉ እንደተላከ ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በትግራይ ክልል ለዜጎች የሚደረገው ድጋፍ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ለተረጂዎች እየቀረበ ያለው ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች ወደ ክልሉ በመላክ ላይ ይገኛል፡፡

አቶ ደበበ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በአየርም ሆነ በየብስ ትራንስፖርት ለዜጎች ሊደርስ የሚገባውን አስፈላጊ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በማመቻቸት ላይ ይገኛል፡፡ ከአጋሮች የሚገኘው ድጋፍ ለሕዝቡ እንዲደርስ በማድረግ በኩል ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ በዚህም ድጋፎቹ ተጠናክረው እየተጓጓዙ ይገኛሉ፡፡





በትግራይ ክልል ያለው ተረጂ አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ መሆኑን የገለጹት አቶ ደበበ፤ ከሐምሌ 15ቀን 2014ዓ.ም እስከ ነሐሴ 3 ቀን 2014ዓ.ም ድረስ ባለው አፈጻጸም፤ 29ሺህ 942ሜትሪክ ቶን ምግብ እንዲሁም 31ሺህ 940 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ወደ ክልሉ በየብስና አየር ትራንስፖርት መጓጓዙን ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ሳምንት ውስጥ ብቻ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚያግዝ 300ሚሊዮን ብር ወደ ክልሉ መላኩንም አቶ ደበበ አስታውቀዋል፡፡ 668ሺህ 506 ሌትር ነዳጅ በዚሁ ሳምንት ውስጥ እንደተላከም ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም 23 ነጥብ 63 ሜትሪክ ቶን መድኃኒትም ወደ ክልሉ መላኩን ጠቅሰዋል፡፡

በዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት (ፋኦ) በኩል ሁለት ሺህ 96 ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ ወደ ክልሉ እየተጓጓዘ መሆኑን በመጥቀስ፤ እስካሁን በዚህ አፈጻጸም ድጋፎቹ እየተደረጉ ያሉት በየብስና በአየር ትራንስፖርት እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ በዚሁ ወቅት መቀሌ የደረሱ ተሽከርካሪዎች ብዛት 983 ሲሆኑ፤ ከዚህ ውስጥ የተመለሱት 328 ናቸው፡፡ ቀሪ 655 ተሽከርካሪዎች አልተመለሱም፡፡

# ያለአግባብ በተዘጋ መንገድና ፍሳሽ ማስወገጃ ለጎርፍ ችግር መጋለጣቸውን ነዋሪዎች ገለጹ

## - ለተጎጂዎች ካሳ ለመክፈልና ችግሩንም ለመፍታት እየሠራ መሆኑን ወረዳው አስታውቋል

**በኃይሉ አበራ እና ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ያለአግባብ በተዘጋ የጎርፍ ማስወገጃ ቱቦ ምክንያት የጤና ችግርና የንብረት መውደም አደጋ እየደረሰብን ነው ሲሉ በአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 5 ልዩ ቦታው አቦ ጨፌ መረዳጃ እድር አካባቢ ነዋሪዎች ገለጹ። ወረዳው በበኩሉ ችግሩ መኖሩን አምኖ ለመፍትሄው እየሠራ መሆኑን ገልጿል፡፡

የጎርፉ ተጠቂና የአካባቢው ነዋሪ ወይዘሪት ሰላማዊት መኩብብ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፣ ከዚህ በፊት ወረዳው በአካባቢው የጎርፍ አደጋ ተጋላጭነትን ለመታደግ ባለሙያ መድቦ ቱቦ መቀበሩን አስታውሰዋል። ከጊዜ በኋላም በአቦ ጨፌ መረዳጃ እድር እና በስፍራው ነዋሪ በሆኑ ግለሰብ ምክንያት መንገድ እና የጎርፍ ማስወገጃ መስመር መዘጋቱ ችግሩን ያባባሰው መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህ የተነሳ ተከራዮችን ሳይጨምር የ16 አባወራ ቤትና ግቢ ለጎርፍ አደጋ ሊጋለጡ ችለዋል። ይህን ጉዳይ ለወረዳው አስተዳደር በተደጋጋሚ ቱቦው እንዲከፈትልን እንጠይቅ ነበር። ነገር ግን አንድም ችግራችንን ሊረዳና ሊፈታ የሚችል አካል ማግኘት ባለመቻላችን በዚህ ክረምት የአስራ ስድስት አባወራዎች ቤት ውስጥ ጎርፍ እየገባ ይገኛል ብለዋል።

በችግሩ የተጎዱት ጎረቤታቸው ቤት ውስጥ የሚገባው ውሃ ጉልበት ላይ እንደሚደርስ የተናገሩት ወይዘሪት ሰላማዊት፣ በሰፈር መዋጮ በተሠራ ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት እየኖሩ መሆኑንም ተናግረዋል።

ክረምት ከገባ ጀምሮ የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ ኮሚሽን ቤት ውስጥ የገባውን ውሃ ዝናብ በተደጋጋሚ እየመጣ እንደሚመጥ ገልጸዋል። በጤናችንና በንብረታችን ላይ የደረሰው በሰው ሕይወት ላይ አደጋ ከመድረሱ በፊት ፈጣን መፍትሄ ሊሰጠን ይገባል ብለዋል። ይህን ተከትሎ አዲስ ዘመን ቅሬታ የቀረበባቸውን ወይዘሮ ታደለች ታዬን አነጋግሯል።

እንደ ወይዘሮ ታደለች ታዬ ገለጻ፣ ከዚህ በፊት በአቶ መኩብብ ታደሰ በኩልና በእኛ በኩል በፍርድ ቤት የወሰን ችካል ሲደረግ የአቶ መኩብብ የሽንት ቤት ማጠራቀሚያ በእኛ በኩል ተገኘ። ይህም ለልጆቼ የጤና ችግር ምክንያት ሲሆን የፍሳሽ መተላለፊያ መስመሩን ዘግቻለሁ። ይህ



ጎርፉ ከተመመጠ በኋላ የተነሳ ፎቶ

በእኔ በኩል የሚያልፈው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር የዝናብ ውሃ ብቻ ሳይሆን የሽንት ቤት ቆሻሻም አብሮ እንደሚያልፍ ጤና መኮንን አረጋግጦልኛል ሲሉም ተናግረዋል።

ወይዘሮ ታደለች፣ የአዲስ አበባ ግንባታና ቁጥጥር ባለስልጣን ፍሳሽ ማስወገጃው አቦ ጨፌ መረዳጃ እድር አቅራቢያ ወደ ሚገኘው ቆሻሻ ማስወገጃ ቢገባ የተሻለ እንደሚሆን አቅጣጫ መስጠቱንም ገልጸዋል። በዚህም አቦ ጨፌ መረዳጃ እድር ሙሉ በሙሉ የፍሳሽ ማስወገጃውን እንደዘጋ አረጋግጧል ብለዋል።

የአቦ ጨፌ መረዳጃ እድር ጸሐፊ አቶ ግርማ አሸናፊ በበኩላቸው፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦውም ለሦስት ዓመታት ያህል አገልግሎት ከሰጠ በኋላም ወይዘሮ ታደለች ታዬ ባቀረቡት ክስ የተነሳ መሆኑን ገልጸዋል።

መረዳጃ እድሩም የተዘጋውን መንገድ እና የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦውን ለማስቀጠል በወረዳው በኩል ካሳ እንደሚከፈል ከተነገረ በኋላ ለማፍረስ የተሰማማ መሆኑን ተናግረዋል።

ወይዘሮ ታደለችም እድሩ ካላፈረሰ አላፈርስም በሚል ኅብረተሰቡ እየተጎዳ መሆኑን ገልጸው፣ ችግሩን በጊዜያዊነት ለመፍታት የገደቡትን ኮንክሪትና ያጠሩትን ቆርቆሮ ቢያነሱ እድሩ ጊዜውን ጠብቆ ከአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በሚላክለት የቦታ ካሳ ሂሳብ መተማመኛ መሠረት የገነባውን እንደሚያፈርስ ገልጸዋል። ለዚህም ዋናው መፍትሔ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ እና ወረዳ አምስት ጋር ነው ብለዋል። ይህን ተከትሎ አዲስ ዘመን የወረዳ 5 ሥራ አስፈፃሚ አቶ በየነ ዘውዱን አነጋግሯል።

የአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 5 ሥራ አስፈጻሚ አቶ በየነ ዘውዱ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፣ አቦ ጨፌ መረዳጃ እድር አካባቢ ከፍተኛ የጎርፍ አደጋ እንዳለ ነዋሪዎች ይናገራሉ። ይህን ችግር ክረምት ከመግባቱ በፊት ለመፍታት ጥረት አድርገናል።

ችግሩንም በዘላቂነት ለመፍታት የፍሳሹ መንገድ በየት በኩል መሄድ እንዳለበት አስጠንተን ጨርሰናል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ ጥናቱ ለሚነካቸው ቤቶችም ተገቢውን ካሳ ለመክፈል ሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል። በዚህ ሳምንት ችግሩ እንደሚፈታም ተናግረዋል።

ችግሩ ያልተፈታበት ምክንያት ወረዳው ወይዘሮ ታደለች ይዞታ ላይ ያለፍቃድ መግባት እንደማይችል በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እገዳ ስለተጣለበት እንደሆነም ተናግረዋል።

ዜና

# ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን ሽብርተኝነትንና የተደራጁ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል ተስማሙ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን ሽብርተኝነትን፣ የታጣቂዎችን እንቅስቃሴና የተደራጁ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል ተባብረው ለመሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ ስምምነቱን የተፈራረሙት የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ እና የደቡብ ሱዳኑ የአገር ውስጥ ደኅንነት ቢሮ ዳይሬክተር ጀነራል አኮር ኮር ኩክ ናቸው።

በስምምነቱ መሠረት በኢትዮጵያና የደቡብ ሱዳን ድንበር አካባቢዎች ሰላምና ፀጥታን ለማደፍረስና የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣናን ለማተራመስ ተልዕኮ ተቀብለው የሚንቀሳቀሱ የሽብር ቡድኖች፣ አማጺ ኃይሎች፣ ታጣቂ ቡድኖችና የተደራጁ ወንጀለኞችን በጋራ ለመቆጣጠርና እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በጋራ ይሠራሉ።

ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሮችን፣ በድንበር



አካባቢ የሚካሄዱ የተደራጁ ወንጀሎችን፣ ሕገ ወጥ የገንዘብ እና የዕጽ ዝውውሮችን፣ የኢኮኖሚ አሻጥሮች እንዲሁም ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን ተቀናጅተው ለመከላከል በመግባቢያ ሰነዱ ላይ ተስማምተዋል።

የተደረሰው ስምምነት ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን ስትራቴጂክ አጋርነታቸውን ይበልጥ በማጠናከር በሁለቱም አገራት፣ በአፍሪካ ቀንድና በአፍሪካ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የደኅንነት ጉዳዮችን የተመለከቱ ወቅታዊ ለውጦች ሲኖሩ መረጃዎችን እንዲለዋወጡና እንዲጋሩ የሚያስችል መሆኑም ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ለኢቢሲ የላከው መረጃ አመልክቷል።

በተያያዘ ዜናም የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ከደቡብ ሱዳኑ የአገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴር የሲቪል፣ የዜግነት፣ ፓስፖርትና ኢሚግሬሽን ምዝገባ ዳይሬክቶሬት ጋር ተባብሮ ለመሥራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነትም ፈጽመዋል።

ሐምሌ 16 ቀን 2014ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን የተመራ የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን ከደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ማያርዲት ጋር አገራቱ ወንጀሎችን በጋራ መከላከል፣ ትብብርን ማሳደግ እና የደህንነት መረጃ መለዋወጥ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ምክክር ማድረጋቸው የሚታወስ ነው።

## «የዓባይ ግድብ ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ግድቡ አሁን ባለው የከፍታ መጠን እያንዳንዳቸው እስከ 270 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ባላቸው ሁለቱ ዩኒቶች አማካኝነት በርካታ ፋብሪካዎችን ወደሥራ ማስገባት የሚቻልበት ዕድል አለ ያሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው፤ ይህ አቅም እያደገ ሲመጣ ደግሞ እንደአገር ያለውን የኢንዱስትሪዎች የኃይል አቅርቦት ችግር ለማስተካከል ሁነኛ አማራጭ እንደሚፈጠር ተናግረዋል።

በተጨማሪ ከግድቡ ውሃ ሙሌት ጋር ተያይዞ በክብደታቸው የተሻሉ የዓሣ ዝርያዎችን በማርባት ምርት ማግኘት ይቻላል። እንዲሁም ግድቡ ሲጠናቀቅ 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ የሚይዝ ሰው ሰራሽ ሐይቅ ስለሚፈጠር ለግብርና ማቀነባበሪያ የሚሆን ከፍተኛ የዓሣ ምርት ግብዓት ለማግኘት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ በግድቡ በፈጠረው ሐይቅ አማካኝነት የውሃ ላይ መዝናኛ አማራጭ ተፈጥሯል። ግድቡ በእራሱ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቱሪስት ለመሳብ የሚያስችል ዕምቅ የቱሪዝም አቅም አለው።

የግድቡን ዘርፈ ብዙ አቅም ደግሞ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማዕድን፣ የቀርከሃና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር አጣምረን ካየነው ተጨማሪ የሥራ ዕድል፣ የኢንቨስትመንትና የመዋዕለ ነዋይ ፍሰትና ዕድገትን በማምጣት ለአገራችን ግዙፍ የኢኮኖሚ አቅም የሚፈጥር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ብለዋል።

በተለይ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ለሰፋፊ እርሻዎች ምቹ የሆነ መሬት፣ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የቀርከሃ ምርት እንዲሁም በርካታ ዓይነት የማዕድን ሀብት ያለበት ስፍራ ነው። በመሆኑም በአካባቢው ካለው ሀብት ጋር የሚጣጣሙ ኢንዱስትሪዎችን በብዛት በመገንባት ግብዓቱንና የኤሌክትሪክ ኃይሉን ማቅረብ ይቻላል ሲሉ አስረድተዋል።

ከዚህ ባለፈ የቱሪዝም ሀብቱን በተገቢው ጥራትና ልክ በማልማት አካባቢውን ዋነኛ የልማት ምንጭ ማድረግ የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ነው። ይህን ሁሉ ሀብት ለማስተሳሰርና ወደኢኮኖሚ ጥቅም ለመለወጥ ደግሞ የዓባይ ግድብ ሁነኛ መሣሪያ ሆኖ ማገልገል የሚችልበት ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አገር በተጽዕኖ ውስጥ ሆነንም ግድቡን መገንባት መቻላችን በእራሱ የሚሰጠን የመንፈስ ጥንካሬም አለ፤ የመንፈስ ጥንካሬው በተለያዩ ዘርፎች ላይ ስኬት እንድናመጣ የሞራል ስንቅ ይሆናል። በቀጣይ ማንኛውም የልማት ሥራችን በውጭ ኃይሎች ተቀባይነት ባይኖረው እንኳን እራሳችን መገንባት እንደምንችል ትልቅ ልምድ የሰጠ በመሆኑ እንደአገር ያለው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንዳስታወቁት፤ ለአገራችን ትልቅ የኢኮኖሚው አቅም ሆኖ ወደሥራ የገባውን ግድብ በተባበረ ክንድ በማጠናቀቅ ይበልጥ አገራዊ ጠቀሜታውን ማሳደግ ይገባል።

## ክልሉ ከማዕድናት ሽያጭ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንቅስቃሴ ላይ ነው ብለዋል፡፡

ክልሉ በዘንድሮ በጀት ዓመት 4 ሺህ 316 ኪሎ ግራም ወርቅ ለገበያ ለማዕከላዊ ገበያ እንዲሁም ለሲሚንቶ ምርት ግብዓት የሚሆን 461 ሺህ ቶን የከሰል ድንጋይ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ማቅረቡን የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፣ ከከበሩ ድንጋዮችና ከሌሎች ማዕድናት ጭምር በጥቅሉ ከ324 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማመንጨት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በአዲስ አበባ ለሚከናወኑ ግንባታዎች ከ22 ሚሊዮን ቶን በላይ የኖራ ድንጋይ ማቅረባቸውን የተናገሩት ኃላፊው፣ በሥራ ዕድል አኳያም በዘርፉ ለ129 ሺህ ሰዎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን አንስተዋል፡፡

በዘርፉ እስካሁን የተደረጉት ጥናቶች ከ10 በመቶ በታች መሆናቸውንና የማዕድናት አስተዳደር መመሪያ ባለመኖሩ ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገት ብሎም ለሕዝቡ ጥቅም የተፈለገውን አስተዋጽኦ እንዳላደረገ አቶ ተስፋዬ ገልጸዋል፡፡

አሁን ግን መመሪያና ደንብ በማዘጋጀት ማዕድን ለማውጣት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ብቻ በሥራው እንዲሳተፉና ማዕድናቱም ተገቢውን ገቢ እንዲያመነጩ እየተሠራ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ባለሥልጣኑ ከተቀመጠው መመሪያ ውጪ የሚንቀሳቀሱ 48 የሚሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሥራ ፍቃድ መሰረዙን ያነሱት አቶ ተስፋዬ፣ በሌላ በኩል በየአካባቢዉ ተደራጅተው መመሪያውን በማክበር ለሚሠሩ በተለይ በወርቅ ማዕድናት ላይ ለተሰማሩ ማህበራት ወርቅን የሚያጥብ 8 ዘመናዊ ማሽኖች ማቅረባቸውን አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ በፊት ማዕድናቱን አውጥተው ከመጠቀም ውጪ ለአካባቢ እንክብካቤና ለሰዎች ደህንነት እምብዛም ትኩረት ስለማይሰጥ ዘርፉ ከሚያደርሰው ጉዳት የተነሳ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደነበር ያወሱት ኃላፊው፣ አሁን ግን የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ ለኅብረተሰብ ልማት ፈንድና አካባቢውን መልሶ ለማልማት የሚውል ከማዕድናቱ ከሚገኘው ገቢ አራት በመቶ ለአካባቢው ኅብረተሰብ እንደሚከፈል ተናግረዋል፡፡

ሆናም ግን በክልሉ ከተፈጠረው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ማዕድን የማውጣት ሥራ ላይ ተጽእኖ መፍጠሩንና በአንዳንድ የክልሉ ዞኖች ታጣቂዎች ማዕድናቱን በመዝረፍ ለጦር መሣሪያ እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል፡፡

በተለይ በጉጂ አካባቢ በጸጥታ ችግር ምክንያት ወርቅ ወደ ማዕከላዊ ገበያ ሳይመጣ በኬንያና በሱማሊያ በኩል ወደውጭ ሲወጣ መቆየቱን አንስተዋል፡፡

ከሕገወጥ ንግድ ጋር ተያይዞ በሕገ ወጥ ንግድ ላይ በመሰማራት መንግሥትና ሕዝብ ማግኘት የነበረባቸውን ገቢ ያሳጡት 20 የውጭ አገር ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን የተናገሩት አቶ ተስፋዬ፣ ለኢኮኖሚ እድገቱ ተመራጭ እየሆነ የመጣውን የማዕድን ዘርፍ ከሕገ ወጥ ንግድና ከታጣቂዎች ዘረፋ ለመታደግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

## መንግሥት ለሰላም መስፈን ያለውን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ፤ መንግሥት የሰብዓዊ ድጋፍ አስተማማኝ እና ዘላቂ በሆነ መንገድ ለማድረስ ይቻል ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎቶችን ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ዳግም ሥራ ለማስጀመር አስቻይ የሆነ ሁኔታ በፍጥነት ለመፍጠርና የሰላም አማራጮችን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት አሳይቷል።

መንግሥት የአገራዊ ምክክር እንዲደረግ ኮሚሽን ከማዋቀር አንስቶ የተለያዩ የሰላም ጥረቶችን ማከናወኑን አስረድተው፤ ለትግራይ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ የበኩሉን ሚና እየተወጣ መሆኑን ተናግረዋል።

የሰላም አማራጭ ዐብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ለጋዜጠኞች በላከው መግለጫ ደግሞ፤ የሰሜኑን ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ በአጭር ጊዜ ላይ መድረስ እንደሚገባ ኮሚቴው አጽኖት ሰጥቶ መወያየቱን አስታውቋል።

የሰላም ሂደቱን ለማፋጠን ይረዳ ዘንድ፣ ወደ ተኩስ አቁም ስምምነት ሊያደርስ የሚችል እና ለቀጣይ የፖለቲካ ውይይቶች መሠረት የሚጥል የሰላም ምክረ ሃሳብ ላይ ውይይት በማድረግ የምክረ ሃሳብ ሰነዱን በማዳበር ማጽደቁንም ኮሚቴው ገልጿል።

ምክረ ሃሳቡ በተቻለ ፍጥነት ለአፍሪካ ህብረት ከፍተኛ ወኪል እንዲቀርብ የሰላም አማራጭ ዐብይ ኮሚቴው መወሰኑ በመግለጫው ተመላክቷል።

በተጨማሪም ኮሚቴው ወደ ተኩስ አቁም ስምምነት ሲገባ በሚፈጠረው አስቻይ ሁኔታ፣ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በተቻለ ፍጥነት መልሶ ማቅረብ ይቻል ዘንድ፣ አስፈላጊ ቅደመ ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆኑን አስታውቋል።

የአፍሪካ ህብረት የሰላም ንግግሩ በአስቸኳይ ተጀምሮ የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ መድረስ ይቻል ዘንድ የሰላም ንግግሩ የሚካሄድበትን ቦታና ጊዜ በፍጥነት እንዲወስን ከኮሚቴው ጋር በቅርበት እየተሠራ መሆኑን ተገልጿል።

ለሰላም አማራጩ ዕውን መሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳየውን ድጋፍ በማድነቅ፣ ይህ ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፤ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ከአፍሪካ ህብረት ጎን በመቆም የሰላም ጥረቱ የተሳካ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ኮሚቴው ጥሪ አቅርቧል።

የሰላም አማራጭ ዐብይ ኮሚቴ በአዲስ አበባ ለሚገኙ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት ማብራሪያ በተሰጠበት ወቅት የፍትሕ ሚኒስትርና የሰላም አማራጭ ዐብይ ኮሚቴ አባል ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ ኮሚቴው ስላከናወናቸው ሥራዎችና ስለሰላም ጥረቶቹ ገለጻ አድርገዋል።

በመድረኩ የዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት እንዲሁም የጠቅላይ የሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትርና የሰላም አማራጭ ዐብይ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ሬድዋን ሁሴንና ሌሎች የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ወጣት ደም ለአሸባሪው ሕወሓት ትንሳኤ የሚቀርብ ርካሽ ደም አይደለም!

አሸባሪው ህወሓት ከውልደቱ ጀምሮ በሴራ ፣ በሀይል እና በክህደት ፖለቲካ የሚታወቅ ፤ ስለ ሰላም ሆነ በሰላም ስለሚገኝ ሀገራዊ ልዕልና ምንም አይነት የአስተሳሰብ መሰረት የሌለው፣ በትግራይ ህዝብ ተስፋና ደም በመቆመር ዘመኑን እየዋጀ ያለ ዘመን ያለፈባቸው ግለሰቦች ስብስብ ነው።

ይህ ቡድን ከውልደቱ ማግስት አንስቶ ስለ ፍትህና ነጻነት ሲሉ ወደ ትግራይ በረሀዎች የገቡ ራሳቸውን ለህዝብ ተስፋ መስዋዕት ለማድረግ የቆረጡ የለውጥ ሰመዓታትን ከማሳደድ ጀምሮ ፤ በሰላም ስም አዘናግቶ በማረድ ይታወቃል። የዚህ ክፉ ልክፍቱ ሰለባ የሆኑ የትግራይ ወጣቶችም ጥቂት የሚባሉ አይደሉም ።

በትግሉ ወቅት የተሻለ አመለካከት ያላቸውን፣ ሀገርን ብሎም የትግራይን ሕዝብ ዘላቂ ተጠቃሚ የሚያደርጉ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ታጋዮችን ከኋላ ከማስመታት ጀምሮ፣ ትግሉን ጥለው እንዲሄዱ የተለያዩ ሴራዎችን በመሸረብ የሚታወቅ ቡድን ነው፡፡ እነዚያ ታጋዮች የጥቂት ግለሰቦች /የአንድ ቤተሰብ / የተበላሸ አስተሳሰብ ሰለባ ሆነው ቀርተዋል ።

ወደ ፌዴራል መንግስት ስልጣን ከመጣ በኋላም ቢሆን ይህ ከውልደቱ የተጠናወጠው የሴራ ፣ የሀይል እና የክህደት ፖለቲካ ሀገርና ህዝብን ከፍያለ ዋጋ አስከፍሏል፤ እድሜያቸውን ሙሉ ለትግሉ የገበሩ የቡድኑ ተዋጊዎችንና ከፍተኛ አመራሮችን ጭምር ብዙ ዋጋ ለከፈሉለት ትግል ባይተዋር እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

በቡድኑ ተራ ፕሮፓጋንዳ ታምነው ቡድኑን የተጠጉ በትጥቅ ትግል ብዙ ዋጋ የከፈሉ እንደ ኦነግ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም በትጥቅ ትግሉ ማግስት በቡድኑ የደረሰባቸው ክህደትና መሳደድ የዚሁ ባህሪው መሳያ ነው። ለፖለቲካ ድራማው ማድመቂያ የፈጠራቸው ፓርቲዎችም በየተራ የደረሰባቸው ክህደት የዚሁ ፍጥረታዊ ማንነቱ መገለጫ ናቸው ።

እንደ ፊውዳሉ ዘመን ፈታውራሪዎች በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሀይልን ከማምለክ ያልተላቀቀው ይህ ቡድን ፣ ባህሪው በፈጠረው ህዝባዊ አመፅ ከሥልጣን በተወገደ ማግስት ተመልሶ በሀይል ወደ ስልጣን ለመመለስ የሄደበት የጥፋት መንገድ ከሁሉም በላይ የትግራይን ሕዝብ ከፍያለ ዋጋ እያስከፈለው ይገኛል፡፡

የትግራይ ህዝብ በቀደመው ዘመን ቡድኑ በፍትህና በነጻነት ስም እየማለ በልጆቹ ደም የተጫወተው ቁማር ከፈጠረው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ስብራት ሳያገግም ፣ልጆቹ በየበረሀው የከፈሉት መስዋእትነት ትርጉም አልባነቱ የፈጠረውን የቁዘማ ሕይወት ሳይሻገር፣ ለተጨማሪ አዲስ መከራና ስቃይ ዳርጎታል።

በትግራይ ወጣቶች ደም "ጦርነትን ባህላዊ ጨዋታ "አድርጎ እስከ ማሰብ የደረሰው ቡድኑ ፣ትናንት ስለ ፍትህና ነጻነት በሚል ባዶ ትርክት የትግይን ህዝብ ያስከፈለው ዋጋ ሳያንስ ዛሬ ደግሞ በትግራይ ወጣቶች ደም ተፈጥሯዊ ሞቱን ለመዋጀት ሁሉንም የጥፋት አማራጭ እየሞከረ ነው።

በአንድ በኩል ለትግራይ ህዝብ ጠላት በመፍጠር ጠላት መጣብህ በሚል ፤ይህ ሳይሳካለት ሲቀር ደግሞ በቡድኑ የጥፋት ተልእኮ የማይሳተፍ ወጣት በክልሉ በቀጣይ የመኖር እጣ ፈንታው ጥያቄ ውስጥ የወደቀ መሆኑን በየአደባባዩ በማወጅ ወጣቱን ለከፋ እልቂት እየመለመለ ይገኛል።

ይህ አይነቱ ወጣቱን ለጦርነት ወይም ለእልቂት የማዘጋጀት የጥፋት ሴራ የቡድኑ የቀደመ ታሪክ አካል ቢሆንም ፤አሁን እየሄደበት ያለው መንገድ ግን የትግራይን ወጣት ከመቸውም ጊዜ በላይ በከፋ መልኩ ለእልቂት የሚዳርግ፣ ሊፈጥር የሚችለውም ማህበራዊና ስነልቦናዊ ቀውስ መራራ ነው ።

ይህንን የቡድኑን የእልቂት መንገድ መላው የትግራይ ሕዝብ ከቡድኑ የፕሮፓጋንዳ ዲስኩር ወጣ ብሎ በሰከነ መንገድ ሊመለከተው ይገባል ። ቡድኑ ከቀደመው ዘመን በከፋ መልኩ በእብሪትና በማን አለብኝነት አሁን ላይ በወጣቱ ትውልድ ላይ እያዘጋጀ ያለው የጥፋት ድግስ ውጤቱ መራራ እንደሚሆን ሊያስተውል ያስፈልጋል።

በትግራይ ወጣቶች ደም "ጦርነት ባህላዊ ጨዋታችን ነው " ለማለት የደፈረ ይህ ቡድን ፤ ሊፈስ ስለሚችለው የትግራይ ወጣት ደም ግድ ይለዋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። የትግራይ ወጣት የተፈጠረው ለቤተሰቡ እና ለሀገሩ ነገዎች ተስፋ ነው። ይህ ተፈጥሯዊ እውነት ነው ። ይህን እውነት ኖሮ ማለፍም የትግራይ ወጣት ግዴታ ነው።

የትግራይ ወጣት ደም ለአሸባሪው ህወሓት ተፈጥሯዊ ሞት ትንሳኤ የሚቀርብ ርካሽ ደም ግን አይደለም ። በፍጹም ሊሆንም አይችልም፤ የትግራይ ወጣት ለቡድኑ ጥይት ማብረጃ እንዲሆን ሆኖ የተፈጠረም አይደለም። የትግራይ ወጣት በርካሽ ፕሮፓጋንዳ ከፍጥረታዊ ማንነቱ እየተፋታ የአንድን ዘመን ያለፈበት ቡድን የማንነት ዲሪቶ የሚሸከም ዜጋም አይደለም!።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአሸባሪው ህወሓት ታሪክ ደደቢት ተጀምሮ ደደቢት የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም

**ዶክተር ጀኔኑስ**

ጌታቸው ሙላቱ የተባሉ አንድ የማህበራዊ ድረ-ገጽ ተጠቃሚ የ«ህወሓት አጭር ታሪክ» በሚል ዘለግ ያለ ግጥማቸው እንዲህ ሲሉ ነበር በመጀመሪያዎቹ ስንኞች ላይ የሰደሩት፡፡

ህወሓት ወያኔዎች፣ ደደቢት ተነሱ፣
ከዚያት ጥቂት ቆዩ፣ አፈር እየላሱ፣
ካሉበት በርሃ፣ በሕዝብ እየተመሩ፣ እየገሰገሱ፣
በሕዝብ የተጠላውን፣ ደርግን አፈረሱ፣
ምኒልክ ቤተመንግስ፣ ገቡና ነገሱ።

እንግዲህ በዚህ ግጥም መግቢያ ላይ ከተጠቀሰው ሃሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው የአሸባሪው ህወሓት ትርክት ስልጣን እና ስልጣን ስለመሆኑ፤ ከደደቢት እስከ አራት ኪሎ የደረሱትም በጀግነንታቸው ሳይሆን በህዝብ እየተመሩ ስለመሆኑ እንጂ በሚዲያ እንደሚደሰኩሩት አለመሆኑ ነው፡፡ አሳዛኙ ነገር ቢኖር ግን በቀጣይ ህወሓት ደደቢት ተፈጥሮ ደደቢት የመቀበሩ እውነታ አሁን አሁን ግልጽ እየሆነ መምጣቱ ነው፡፡

በርካታ ህወሓታውያን በአንድም ይሁን በሌላ በሕይወት ዘመናቸው ከቡድኑ ውጪ እንዳይሳቡ በመደረጉ ቡድኑን እንደጣዖት የመመልከት እርግማን ውስጥ ገብተዋል። ይህ ከትግራይ ህዝብ መንፈሳዊ፣ባህላዊና ማህበራዊ የልቦና ውቅር የተጣላ አስተሳሰብ ከነሱ አልፎ የትግራንም ህዝብ ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል።

ቡድኑን እንደ ጣዖት የሚመለኩ ግለሰቦች መጨረሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ ባይሆንም፤ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የፖለቲካ መድረክ ውስጥ አንድን ቡድን ጣኦት አድርጎ የመቀበሉ አውነታ በብዙ መልኩ ከማሳዘን አልፎ የሚያሳፍር፤ ከዘመን ጋር በዓደባባይ ተጣልቶ መገኘትን አመላካች ነው ።

ኃይል አምላኪነት የተጠናወተው፤ ከውልደቱ ጀምሮ የጦርነት ከበሮ በመደለቅ በትግራይ ወጣቶች ደም የሚቆምረው ይህ ቡድን በፕሮፓጋንዳው ዛሬም የትግራይን ወጣት ለዳግም እልቂት እያነሳሳ ይገኛል። ለሰላም የተሰጠውን ዕድል ትርጉም ለሌለው እብሪት አሳልፎ በመስጠት የትግራይን ህዝብ እንደህዝብ ያልተገባ ዋጋ ለማስከፈል የጦርነት ከበሮ እየደለቀ ይገኛል። ለዚህ አስገዳጅ በሆነ መልኩ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ቢቢሲ ግንቦት 04 ቀን 2022 በሠራው ዜና እንዲህ ብሎ ነበር ርዕስ ሰጥቶት ነበር፡፡ «ህወሓት ለመዝመት ፍቃደኛ ያልሆኑ ልጆች ወላጆችን እያሰረ መሆኑ ተነገረ» ይላል፡፡ ህወሓት እየተካሄደ ባለው ጦርነት ልጆቻቸው ያልዘመቱ ወላጆችን እያሰረ እንደሚገኝ የቤተሰብ አባላት ለቢቢሲ ተናገሩ በሚለው ዜናው፤ ቢቢሲ ያነጋገረው አንድ የትግራይ ተወላጅ፣ልጆች ለመዝመት ፍቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ወላጅ አባቱ እና አጎቱ ታስረዋል፡፡ «ቢያንስ ከቤተሰብ አንድ ሰው ውትድርና መላክ አለበት፤ መዋጣት አለበት የሚል ሕግ አለ» ይላል ታዳጊው።

ይህ በአሁኑ ወቅት ከትግራይ ክልል ውጪ የሚገኘው ወጣት፤«አባቴን ልጅህን አምጣ አሉት። ማምጣት ስላልቻለ ለአንድ ወር አሰሩት። ከዚያ ደግሞ ወንድሜን እንዲያመጣ ብለው ለቀውት ነበር። አሁን ያለበትን ሁኔታ ባላውቅም ለመጨረሻ ጊዜ በስልክ ሳገኛቸው አባቴን አስረውት ነበር»በማለት በዚያ አካባቢ ያለውን ሰቆቃ አስረድቷል።

ወጣቱ እንደሚለው አዋቂ የሆነው ወንድሙ በዚህ ጦርነት ተሳታፊ የመሆን ፍላጎት የለውም። «ወንድሜ እኮ ትልቅ ነው። ከፈለገ የአባቴን ፍቃድ ሳይጠይቅ ይሄድ ነበር። የያዙት ግን አባቴን ነው» ሲል የትግራይ ወጣት ለእሳት ለመማገድ ደፋ ቀና የሚለው አሸባሪው ህወሓት የሚይዘው የሚጨብጠው ሁሉ እንደጠፋው ያሳያል፡፡ ልጆቻቸውን ወደ ጦር ሜዳ ባለመላካቸው አጎቱም ጭምር ለእስር ተዳርገዋል፡፡ 18 ዓመት ያልሞላቸው ታዳጊዎችን ጭምር ወደ እሳት ማግዱ እየተባሉ እየተገደዱ ስመሆኑ እጃቸውን ለአማራ ክልል ፀጥታ ኃይሎች፣ ለአገር መከላከያ ሰራዊት እና ፋኖ የሰጡ የትግራይ ተወላጆች ይናገራሉ፡፡ ቡድኑ ከሠላማዊ ህይወት ይልቅ የጦርነት ጥማት ያለበት ቡድን ነው ፡፡ የቀደመ ታሪኩም በአብዛኛው የሚያሳየው ይህንኑ ነው።

በፌደራል መንግስት ስልጣን ላይ በነበረባቸው 27 ዓመት በትግራይ ህዝብ ጫንቃ ላይ በመሆን ህዝቡን ከሌላው ኢትዮጵያዊ ሊነጥለው ሞክሯል፡፡ በሐሰት ትርክት ጀግና ለመመስል እና እንደእርሱ የነበዙ ጀግኖችን ለመፍጠር ሲቃዥ ቆይቷል፡፡ ከቡድኑ የአሸባሪነት ባህሪው በመነሳትም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናው ሥጋት ስለመሆኑ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ ህወሓት ኢትዮጵያን ማቃናት ሳይሆን ኢትዮጵያን እየቦጠቦጠ ራቁቷን ያስቀረ ነው፡፡ በህገወጥ የንግድ ስርዓት በመሰማራት በሀገሪቱ ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ በባህር ላይ ውንብድና ሆነ በሌሎች ህገወጥ ተግባራት ውስጥም ሹማምንቶቹ ተሳትፈው ተገኝተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋ በገንዘብ ሚኒስቴር እና ብሄራዊ ባንክ ከሚዘወረው በላይ በህገወጥ ደላሎችና ኢኮኖሚውን ያለአግባብ ሲያንቀሳቅሱ የነበሩ ኪራይ ሰብሣቢዎችም የህወሓት ቁንጮ ሰዎች ነበሩ፡፡ ኢኮኖሚው፣ የሀገሪቱ ማህበራዊ ስሪትና ፖለቲካው ህጋዊ ከመሆን በላይ ከህግ ውጭ አፈንግጦ በደባና ተንኮል እንዲመራው ህወሓት ጠንሳሽ ዋነኛ ተዋናይ ነው፡፡

በመንግስት ስልጣን ከለላ በማድረግ ከኢኮኖሚው ከአቅም በላይ የመጠቀምና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዳይኖር በማድረግም የአንበሳውን ድርሻ ይዞ የቆየ የማፍያ ቡድን ስለመሆኑም የጥቃቱ ሰለባዎች በየአደባባዩ የሚመሰክሩት ሀቅ ነው፡፡

በዚህ ሁሉ ቅሌት የነወረው ይህ ማፍያ ቡድን፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ላይ በተኛበት ጥቃት በማድረስ የመጨረሻ የተባለውን የሀገር ክህደት ፈጽሟል፡፡ ጥቃቱን ተከትሎ በመንግስት በተካሄደው የህልውና ዘመቻ አብዛኞቹ የቡድኑ አመራሮች ሙት ሆነዋል፡፡ ከፊሎቹም በቁጥጥር ስር ውለው የፍርድ ሄደታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ።

መንግስት የቡድኑ እብሪት በትግራ ህዝብ ላይ ያስከተለው እና ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት) ሠላማዊ ህይወት እንዲመሩ፤ የዘር ጊዜም እንዳያመልጣቸው (በሚል የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከክልሉ እንዲወጣ ቢያደርግም የቡድኑ ርዝራዥ ዳግም በመሰባሰብ በአፋር እና አማራ ክልል ወረራ በመፈፀም ዳግም ዳግም ወደ አራት ኪሎ ያደረጉት ጉዞ በብዙ ኪሳራ ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡ በወቅቱም በቡድኑ ላይ ከደረሰው መጠነ ሰፊ ኪሳራ የተነሳ ከፍባለ ድምጽ ስለ ሰላምና ድርድር እንዲጮህ ያስገደደው ቢሆንም ፤ውሎ ሳያድር ተመልሶ የጦርነት ከበሮ ወደመጎሰሙና የትግራን ወጣት ለእልቂት ወደ መመልመሉ ተመልሷል። መንግስት ያለ ቅድመ ሁኔታ ወደ ድርድር ለመግባት ለደረሰበት ውሳኔም ቅድመ ሁኔታዎችን ወደ ማስቀመጥ ሄዷል።

ከፍጥረቱ ጀምሮ በሰላማዊ ንግግርና ድርድር የማያምነው አሸባሪው ህውሓት ፤የመንግስትን የሰላም መሻት ጊዜ መግዢ ለማድረግ እየመከረ ነው። ለዚህ ደግሞ በህግ መላው የትግራይ ወጣት መሳሪያ አንስቶ ለቡድኑ ህልውና እንዲሞት እያስገደደ ይገኛል። በቅርቡ የቡድኑ ሊቀመንበር ዶክተር ደብረጺዮን «ለጦርነቱ ጥሪ ምላሽ የማይሰጥ ወጣት ወደፊት በሚወጣ ህግ የሚያጣቸው መብቶች እንዳሉ በአደባባይ አሳውቋል።

አሸባሪው ህውሓት ለድርድር ያስቀመጣቸው / ሊያስቀምጣቸው የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ሊኖሩ አይችሉም። «ላም አለኝ በሰማይ፤ወተቷን አላይ» ከልሆነ በስተቀር ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ የሚያስችል ወቅታዊ ቁመናም የለውም፡፡

ትልቁ ነገር የህወሓት ርዝራዢች አሁንም ወደ ጦርነት በመግባት የትግራይን ወጣት ለዳግም እልቂት ሊዳርጉት ይፈልጋሉ። ይህ ደግሞ እንደቀደሙት ወቅቶች አልጋ በአልጋ የሚሆን አይደለም። የትግራይ ወጣት ትርጉም አልባ ለሆነ ጦርነት እራሱን የመስዋእት በግ አድርጎ የሚሰጥበት የንቃተ ህሊና ውድቀት ውስጥ አይደለም።

በከበሮ ድለቃና በሆሆይታ ዘፈን ሕይወቱን ዘመን ላለፈባቸው፤ ዛሬም በትግራይ ወጣት ደም ነገዎቻችውን ተስፋ ለሚያደርጉ፤ በንጹሀን ደምና በትግራይ ህዝብ ተስፋ ለደለቡ መስዋእት አድርጎ አይሰጥም፡፡ ለዚህም ነው ለህወሓት የጦርነት ጉሰማና ቅስቀሳ ጆሮ በመንፈግ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደ አጎራባች ክልሎች እየፈለሱ ያሉት፡፡ ሕይወታቸው ከቡድኑ የፕሮፓጋንዳ ትርክት በላይ ዋጋ እንዳለው በተጨባጭ እያሳዩ ያለው።

የተቀረው ቢሆን እዚያው ትግራይ ክልል ውስጥ ሆኖ እንቢታውን እየገለፀ ነው፡፡ይህ የዛሬው የትግራይ ወጣት እንቢታ፤ የነገውን የትግራ ህዝብ እጣ ፈንታ የሚቀይር ፤ህዝቡ እንደ ህዝብ በሰላም የመኖር ተፈጥሯዊ መብቱን የማስጠበቅ አልፋና ኦሜጋ ነው። ይህን አጠናክሮ መቀጠል ደግሞ እውነተኛ የሆነውን የነፃነት ቀን ማፍጠን ነው።

ትልቁ እውነት አሸባሪው ህወሓት ትግራይን በሰላማዊ መንገድ ሊመራ ቀርቶ ራሱን ማዳን የማይችልበት ደረጃ ላይ ነው፡፡ የትግራይ እናቶች፣አባቶችና ወጣቶች በጀመሩት መንገድ እንቢታቸውንም ማቀጣጠልና ህወሓትን እስከመጨረሻቸው ማሠናበት አለባቸው፡፡

ትግራይ ሠላምን እንጂ ፀረ-ሠላሞችን የምትሸከምበት ጫንቃ እንደሌላት ታሪክ በመሥራት ማሳየት አለባት፡፡ ከእንግዲህ ከህወሓት በኩል ለሚሰነዘር ጥቃት ዝምታን የሚመርጥ ኢትዮጵያዊ መኖር የለበትም፡፡ የአሸባሪው ህወሓት ታሪክም ደደቢት ተጀምሮ ደደቢት ስለመፈፀሙ በትክክል ማረጋጥም የመላው ኢትዮጵውያን ትልቅ ኃላፊነትና ታሪካዊ ድርሻ ነው፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## አሸባሪው ህወሓት ቅድመ ሁኔታ የሚደረድረው እጁ ላይ ምን አለውና ነው .!?

አሸባሪው ህወሓት እድሜ ዘመኑን ከህደት የተጣባው ፤ በመታመን ኪሳራና እዳ እስከ አንገቱ የተዘፈቀ ሆኖ እያለ መንግስት ለሀገርና ለሕዝብ ሰላም ሲል የወይራ ዝንጣፊ ይዞ እጁን ሲዘረጋለት አንድ ጊዜ ቅድመ ሁኔታ እየደረደረ ፤ ሌላ ጊዜ የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ የሚያንገራግረው በምንና በማን ተማምኖ ነው። ቅድመ ሁኔታ ለመደርደርስ ምን መደራደሪያና ጫና መፍጠሪያ/leverage/እጁ ላይ አለ ፤ ጦርነትን እንደ ጣኦት ከማምለክ ውጭ ፤ የትግራይ ሕዝብ እንዲሁ በደጀንነት ፋቲግ የተሰላቸና የተዳከመ ፤ ሰራዊት የውጊያ ሞራሉ የተንኮታኮተ ፤ የትጥቅና የስንቅ እጥረት ክፉኛ ያቆራመደው ፤ ከዚህ ቀደም በለኮሳቸው ጦርነቶች ከፍተኛ የጦር መሪዎችን፣ ሰራዊቱንና የጦር መሳሪያውን በተለይ ከባድ መሳሪያውን ያጣ ፤ የሚያካሂደውም ሆነ ያካሄደው ውጊያ አላማ የሌለው፤ ለአንድ ጦርነት ወሳኝ ግብዓት የሆነው ሎጂስቲኩ አከርካሪው የተሰበረበት፤ ወዘተረፈ ሆኖ እያለ ታዲያ እንዲህ ለያዥ ለገናዥ የሚያስቸግረው ለምንድን ነው!?

በአንጻሩ የኢትዮጵያ መንግስት ሰራዊት የሚዋጋው ሀገሩ በታሪካዊ ጠላቶቿና እንደ ህወሓት ባሉ ተላላኪዎች እንዳትፈርስ የሚል የተከበረና የተቀደሰ ጽኑ አላማ አንግቦ ፤ በየጊዜው የሚሰለጥንና የነፍስ ወከፍም ሆነ የቡድን መሳሪያ እስካፍንጫው የታጠቀ ፤ ሰራዊቱም ሆነ አመራሩ በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራና የዕዝ ጠገጉን የሚያከብር ፤ በሜካናይዝድ፣ በአየር ኃይል ፣ በዘመናዊ የመገናኛ ዘዴና ድሮን የሚታገዝ ፤ አስተማማኝና ቀጣይ የትጥቅ ፣ የስንቅና የሰራዊት አቅርቦት ያለው ፤ ለሀገር ህልውናና ሉዓላዊነት ሲል ተገዶ የገባበት ፍትሐዊ ጦርነት ነው ።

ከአሸባሪው ህወሓት አንጻር ሲታይ ጦርነቱን የመሸከም ኢኮኖሚያዊ አቅም ያለው ፤ እንደ አባቶቹ ቀፎው እንደተነካ ንብ ለሀገሩ በአንድነት ሆ ብሎ የሚነሳ 115 ሚሊየን ሕዝብ በደጀንነት ያሰለፈ ፤ ወዘተረፈ ስለሆነ ለመደራደር አብላጫ ጉልበት/leverage/ያለው መንግስት ሆኖ እያለ ህወሓት ለምን ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል !? መልሱ ቀላል ነው ። ከጦርነቱ በፊትም ሆነ በኋላ የዐቢይ አስተዳደር ለሰላም ያለውን የማያወላውል ቁርጠኛ አቋም ቡድኑ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በሚያሳዝን ሁኔታ ይሄን የመንግስት ጥንካሬ እንደ ድክመት ቆጥሮ ነው ቅድመ ሁኔታን እየደረደረ ያለው ። ለህወሓት ለሰላም መጨነቅና መጠበብ ድክመት ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ትግራዋይ ጦርነት ይበቃቸዋል፤ የሚያስፈልጋቸው ልማትና ብልጽግና ነው ማለት ለህወሓት እንደ ፍርሃት ነው የሚቆጠረው ።

ሀገራችን የጦርነትን ቀለበት ሰብራ መውጣት ስላለባት ፤ ጦርነት የሀገርን ኢኮኖሚ የሚያንኮታኩት፤ ሀገርን ከልማት ከዕድገትና ከብልጽግና የሚያስተጓጉል፤ ዜጋን በተለይ አምራቹን የሰው ኃይል የሚያስጨርስ ፤ በጦርነት ዘላቂ ሰላም እንደማይመጣ፤ በተለይ የእርስ በርስ ጦርነት አሸናፊ የሌለውና የዜሮ ድምር ፓለቲካ አጫፋሪ ስለሆነ ፤ ህወሓት አመጣሹ ማባሪያ የሌለው የትግራይ ሕዝብ ኀልቆ መሳፍርት የሌለው መከራና ስቃይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ ጽኑ ዕምነት ስላለው ፤ ከአሸባሪው ህወሓት ይልቅ መንግስት ለአለምአቀፍ ሕጎችና ለሞራል ልዕልና የሚገዛ ፤ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት መሆኑ እና ስለነገዋ ኢትዮጵያ ብሩሕ ተስፋ የሰነቀ መንግስት ስለሆነ ይህ ተስፋው እንዲጨናገፍ ስለማይፈልግ ወደ ግጭትም ሆነ ወደ ጦርነት የመግባት ምንም ፍላጎት የለውም ።

አሸባሪው ህወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ ትውልድም ሆነ ታሪክም ይቅር የማይለው ጭፍጨፋና ክህደት እስኪፈጸመ ድረስ መንግስት ህወሓትን ወደ ሰላም ለማምጣት ያደረገውን ተደጋጋሚ ጥረት የሚዘነጋ አይደለም ። ሆኖም ሰላም በአንድ ወገን ጥረትና ፍላጎት ብቻ እውን አይሆንምና ከአንድ ጊዜም ሁለት ጊዜ ውድ ዋጋ አስከፍሎናል ። መንግስት ዛሬም ህወሓትን እሽሩሩ የሚለውና ለሰላም ያለ ምንም ቅድመ ሆኔታ ረጅም ርቀት እየሄደ ያለው ጦርነትን ለማስቀረት ነው። የሚያሳዝነው ህወሓት መንግስት ምን ያህል ለሰላም ቁርጠኛ እንደሆነ ስለሚያውቅ ይሄን ክፉኛ የመንግስት መሻት ገልብጦ እንደ መደራደሪያ አቅም/ሌቨሬጅ/እየተጠቀመበት ይገኛል ።

መንግስት ለሰላም ሲል የማቀርብለትን ቅድመ ሁኔታ ሁሉ ያለ ማመንታት ይቀበላል የሚል የተሳሳተ ዕምነት ይዟል ። ለዚህ ነው መንግስት በአንድ ወገን ፍላጎትና ጥረት ሰላም እንደማይመጣ በተደጋጋሚ ገጥሞት አይቷልና ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል የሚባለው። ሆኖም ለሰላም ያሳየው ቁርጠኝነት ሁሉ በዜሮ ተባዝቷል ማለት አይደለም ። ምንም እንኳ አጥጋቢ ባይሆንም ምዕራባውያንና አለምአቀፉ ማህበረሰብ ስለ መንግስት የነበረውን ሸውራራ አመለካከት መለስ ብሎ እንዲያጤን ፋታ መስጠቱ አልቀረም ። አቋማቸው በተወሰነ ደረጃ እየተለሳለሰ መምጣቱን እየታዘብን ያለው ለዚህ ነው ። ይሁንና መንግስት ከሚገባው በላይ ለዛውም በተናጠል ነገረ ስራውና ሰራ አካላቱ ሁሉ ለሰላም መወሰዱ/obsessed/መሆኑ ከገደቡ እንዳያልፍ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል ።

በቅድመም ሆነ በድህረ ጦርነት ህወሓትን ሲያስፎክሩና ያዙኝ ልቀቁኝ ሲያስብሉ የነበሩ የመደራደሪያ አቅሞች አንድ በአንድ ከእጁ እየወጡ አጨብጭቦ እየቀረ ነው ። ለውጡ እንደባ'ተ ኮሽታ ሳያሰማ ጭራውን ቆልፎ ተጠራርቶና ተጠቃቅሶ ወደ መማጸኛ ከተማው መቀሌ በፍጹም ራስ መተማመንና ዕብሪት የመሸገው ላለፉት 50 አመታት ያጠመዳቸውን ፈንጅዎች ማቀጣጠያ ፊውዞች ተማምኖ ነበር ። ላለፉት አራት አመታት እነዚህን ፊውዞች አንድ በአንድ እያየያዘ የስልጣን ጥሙን ለመቁረጥ ያደረገው ጥረት ሁሉ ሲከሽፍ ደግሞ እንደ ወሼ እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል በሚለው የልቦና ውቅሩ እኔ እንደ ብረት ቀጥቅጬ የማልገዛትና የማልዘርፋት ሀገር ትፍረስ ብሎ የሄደበት መንገድም ምንም እንኳ ውድ ዋጋ ቢያስከፍለንም ተቀልብሷል ። ከህወሓት እጅ አንድ በአንድ ያመለጡ የመደራደሪያ አቅሞችን ወይም ነጮች እንደሚሉት "ሌቬሬጅስ" እስኪ መለስ ብለን በስስ በስሱ እንቃኝ ።

አሸባሪው ህወሓት ከምንም በላይ ሲመጻደቅበትና ሲኩራራበት የነበረው የውጊያ ብቃቱን ነበር ። በአደባባይና በሸንጎ በአፍሪካ ህወጋትን በጦርነትና በውጊያ ስልት የሚያክለው የለም እያለ እንደ መንደር ጎረምሳ ያዙኝ ልቀቁኝ ይልበት የነበረው ዕብሪቱ የሰሜን ዕዝ በተከዳና በተጨፈጨፈ ማግስት ሶስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አከርካሪው ተሰብሮ ቆላ ተምቤን ሊወርድ ችሏል ። ምንም እንኳ መንግስት በተከተለው የተሳሳተ መንገድ ድሉን ማስጠበቅ ፣ ማጽናትና ማዝለቅ ባለመቻሉ አፈር ልሶ ተነስቶ ያልተገባ ዋጋ ቢያስከፍለንም ። በሁለቱም ጦርነት ከፍተኛ ፓለቲካዊና ወታደራዊ አመራሮችን ፣ ሰራዊቱን ፣ የጦር መሳሪያውን፣ የውጊያ ሞራሉን ፣ ወዘተረፈ አጥቷል ።

> **በቅድመም ሆነ በድህረ ጦርነት ህወሓትን ሲያስፎክሩና ያዙኝ ልቀቁኝ ሲያስብሉ የነበሩ የመደራደሪያ አቅሞች አንድ በአንድ ከእጁ እየወጡ አጨብጭቦ እየቀረ ነው ። ለውጡ እንደባ'ተ ኮሽታ ሳያሰማ ጭራውን ቆልፎ ተጠራርቶና ተጠቃቅሶ ወደ መማጸኛ ከተማው መቀሌ በፍጹም ራስ መተማመንና ዕብሪት የመሸገው ላስፉት 50 አመታት ያጠመዳቸውን ፈንጅዎች ማቀጣጠያ ፊውዞች ተማምኖ ነበር**

ዛሬ የህወሓት የውጊያ ብቃት ከአራትና ከሶስት አመታት በፊት እንደነበረው የመደራደር አቅም ሊሆን ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል ። ይህን ስል እንዘናጋ እያልሁ አይደለም ። ህወሓት ነገ ምን ፈጥሮና አድርጎ ሊያስደነግጠንና ሊያስደንቀን እንደሚችል መገመት ይቸግራልና ። ሆኖም ከህወሓት ማንነትና ባህሪ ተነስቶ የማይጠበቀውን ለመጠበቅ በስነ ልቦናም በአካልም መዘጋጀት ይገባል ። ህወሓት ለሰላም እንዲያ እግሩ ላይ ተወድቆ ሲለመን ይጓደድ የነበረበት ሌላው ምክንያት ላለፉት 50 አመታት በተለይ ደግሞ ላለፉት 30 አመታት ተቋማዊና መዋቅራዊ አድርጎ ሲዘራውና ሲኀነቁለው የኖረው የዘረኝነት የጎሰኝነት የልዩነት የጥላቻና ቂም በቀል ፈንጂ ፊውዝን በፈለገ ጊዜ በቀላሉ እያይዞ አማራው ከኦሮሞው ፣ አፋሩ ከኢሳው፣ ሲዳማው ከወላይታው፣ ሱማሌው ከኦሮሞው ፣ አማራው ከጉምዙና ከቅማንቱ ሲባላና ሲጫረስ ሀገር ወደ ለየለት የእርስ በርስ ግጭት ስትዘፈቅ የዛን ጊዜ በአቋራጭ አገዛዝ ላይ መመለስ ነበር የቀን ቅዠቱ ።

ባለፉት አራት አመታት በዚህ የህወሓት መሠሪ ዳባ ከሰሜን እስከ ደቡብ ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ንጹሐን በግፍ ቢጨፈጨፉ ፣ ሀብት ንብረታቸው ተዘርፎ ከቀያቸው ቢፈናቀሉም በሀዘን ቅስማችን ቢሰበርም ፤ በሆነው ሁሉ ጥርሳችንን ብናፋጭም ፤ በአለም አደባባይ አንገታችንን ብንደፋም ፤ በሀዘን ከል ብንለብስ፣ በራሳችን ትቢያ ብንነሰንስም ፤ በኢትዮጵያ አምላክ ምህረት ወደ ማያባራ የእርስ በርስ ጦርነት አልገባንም ፤ ህወሓትም እኛን አባልቶ ወደ አገዛዝ አልተመለሰም ። አይመለስምም ። ዛሬ ከሶስትና አራት አመታት በፊት ከነበረው በብዙ እጥፍ የተሻለ የጸጥታና የደህንነት ተቋም መገንባት ስለቻልን ፤ የህወሓት ክፉ ሀሳብ ከማይሳካበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ። የመደራደሪያ ጉልበቱ የነበረው የ50 አመት ፕሮጀክቱ በዚህ መንገድ ከሽፏል ።

አልሻባብ ፣ ሸኔ ፣ የቅማንት የጉምዝ የጋምቤላና የአገው ታጣቂዎች ሌላ የህወሓት የመደራደሪያ ጉልበቶች ነበሩ ። እነዚህን ቡችሎቹን እስፖንሰር እያደረገ ስምሪት በመስጠት አገር በአራቱ ማዕዘናት እንደ ሌጦ ስትወጠር ህወሓት የጎበዝ አለቃ ሆኖ ራሱን ለመሾም አሰፍስፎ የነበር ቢሆንም ይሄም እንደ ቀን ቅዠቱ መሻት አልሆነም ። ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደ ሞከርሁት የለውጥ ኃይሉ ምንም ጊዜ ሳያጠፋ በጸጥታና በደህንነት ተቋማት ላያ ያደረገው ማሻሻያ ቆይቶም ቢሆን እየከፈለው ይገኛል ። ሰሞኑንና በአልሻባብ ላይ ያረፈው ብርቱ ክንድ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው ። እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ተሞክሮ የጠራ የፓለቲካና የጸጥታ ተቋም ክልል ላይ ሲኖር ከፌደራል መንግስት ጋር ተቀናጅቶ ምን አይነት ተአምር ሊፈጥር እንደሚችል በሱማሌ ክልል እየተመለከትን ነው ።

በአደባባይ ባያውጅም እንደ መደራደሪያ ጉልበት ወይም ሌቬሬጅ ከሚጠቀምባቸው ኃይሎች በታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ያኮረፉት ግብጽና ሱዳን ይገኙበታል ። ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጎን በመቆም የሚታወቀው ህወሓት የዛድባሬን ወረራ ደግፎ ከታላቋ ሶማሊያ ፕሮጀክት ጎን ተሰልፎ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም የግብጽን ሀገራችንን የማተራመስና የማፍረስ ተልዕኮ ወስዶ የሕዳሴውን ግንባታ ለማጨናገፍ ሌት ተቀን ሲማስን ከርሟል ። ለዚህ ውለታው ደግሞ የዲፕሎማሲ ፣ የፓለቲካ ፣ የሚዲያ ፣ የቅጥረኛና የፋይናንስ ድጋፍ ሲደረግለት ቆይቷል ። ይሁንና ግብጽ ይሄ መንገዱ እንዳልተሳካ የሕዳሴው የውሃ ሙሊት ለ3ኛ ጊዜ ያላንዳች መስተጓጎል መካሄዱና ከአንድም ሁለት ዩኒቶች ኃይል ማመንጨት መጀመራቸው ጮኸ ብለው ይናገራሉ ።

ግብጽ እንደ ህወሓት ያሉ ከሀዲ ተላላኪዎችን የትም እንደማያደርሳት እየተረዳች ስለሆነ ለእነዚህ የእናት ጡት ነካሾች ስታደርግ የቆየችው ዙሪያ መለስ ድጋፍ በነበረበት አይቀጥልም ። ህወሓት ሱዳን በግብጽ አይዞሽ ባይነት ድንበራችንን አልፋ መሬታችንን ስለወረረች የኢፌዴሪ መንግስት በደም ፍላት ጦርነት ውስጥ ሲገባ ግብጽ ከሱዳን ጎን ስለምትቆም በዚህ ግርግር ለማትረፍ ቋምጦ የነበረው ህወሓት ሳይሳካለት ቀርቷል ። እንዲህ እንዲህ እያልን ከወጭ ቀሪ ስንተሳሰብ ህወሓት ቅድመ ሁኔታ ለመደርደር እንደ አቅም የሚታይና ይህ ነው የሚባል ሌቨሬጅ እንደሌለውና ባዶ እጁን አጨብጭቦ እንደቀረ እንረዳለን ። ምንም እንኳ ከስህተቱ የመማር መርገም እንዳለበት የሚታወቀው ህወሓት ይሄን ሀቅ ተገንዝቦ ወደ ድርድሩ ይመጣል ተብሎ ስለማይጠበቅ መንግስት ለማንኛውም ነገር ቆቅ ሆኖ መጠበቅ አለበት።

**ሀገራችን ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር ! አሜን ።**

# ‹‹የመውጫ ፈተናው ለወደፊት በገበያው የትኞቹ የትምህርት ክፍሎች እንደሚዘልቁ ይነግረናል››

**- ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ**
**የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ**

**ዘላለም ግዛው**

በ2015 ዓ.ም ይተገበራል ተብሎ የሚጠበቀው የዩኒቨርስቲዎች የመውጫ ፈተና በብዙዎች ዘንድ አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኗል። የትምህርት ጥራትን መግቢያ ላይ እንጂ በመውጫ በሚሰጥ ፈተና ማረጋገጥ አይቻልም ፤ የትምህርት ሚኒስቴር ፈተናውን ለመስጠት የሚያስችል የሕግ መሰረት የለውም የሚሉና ሌሎች አስተያየቶች ይሰነዘራሉ። በእነዚህና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ ጋር ያደረግነው ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን:- በዩኒቨርስቲዎች የመውጪያ ፈተና ለምን አስፈለገ ? ከመቼ ጀምሮስ ተግባራዊ ይደረጋል? ከዚህ ጋር ተያይዞስ ምን ያህል አመኔታ ይኖረዋል ?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** የመውጫ ፈተና የተማሪዎቹን ውጤታማነትና በትምህርት ጥራት ውስጥ ያለውን ስብራት ለመፍታት ከሚወሰዱ እስትራቴጂያዊ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ ሆኖ ይተግበር የሚለው ውሳኔ የቆየ ነው። ሆኖም ግን በተለያየ ምክንያት ላለፉት 11 ዓመታት ተግባራዊ የሆነው በጤናና በሕግ ትምህርት ላይ ብቻ ነበር። በሌሎቹ ዘርፎች ላይ በ2010 ዓ.ም ሂደቱ ተጀምሮ 2011 ዓ.ም ይተገበራል ተብሎ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ በተለያዩ አገራዊ ምክንያቶች እንዲቆይ ተደርጓል።

በጤናውም በሕግ ትምህርት ፈተናዎች ያለፉት 11 ዓመታት ሲተገበር አቅም ተገንብቷል፣ ልምድ ተቀስሟል፣ ስህተቶች ተፈጥረው ከሆነም ትምህርት ተወስዶበታል። ይሄ አዲስ ሪፎርም አይደለም።

ተግባራዊ የተደረጉት የጤና እና የህግ የመውጫ ፈተናዎች የሚሰጡት በተለምዶ አሰራር በወረቀት ፈተና ነው። ፈተና ማዘጋጀት፣ ማጓጓዝ፣ መሰብሰብ፣ በእጅ ማረም የራሱ የሆነ ክፍተት አለው።

በሕግ ደግሞ በራሱ በትምህርቱ ባህሪ ምክንያት አንድን የተማሪ ወረቀት ሶስት ሰው ያርመዋል። ሕግ የክርክር ጉዳይ ስለሚሆን ሶስቱ መምህራን ተመሳሳይ ውጤት ላይሰጡ ይችላሉ። አንዳንዴ በጣም የተራራቀ ውጤት ይሰጣሉ። አንዱ አራሚ ተፈታኙ ለሰጠው የክርክር ሃሳብ ብላሽ ነው ብሎ አንድ ነጥብ ሊሰጥ ይችላል፣ ሌላኛው አራሚ ደግሞ ጥሩ የክርክር አንግል ነው ብሎ በተቃራኒው ከፍ ያለ ነጥብ ሊሰጥ ይችላል። ይሄ የሚፈጥረው ልዩነት ቅሬታ ይፈጥራል። በዘፈቀደ የታረመ ያስመስለዋል። የፈተናው ተጨባጭ አለመሆን ችግር ነበረው። ጥቂትም ስህተት ስርዓቱን ከረበሸው ውጤቱ በሰው ነው የተስተካከለው ሊባል ይችላል። በመሆኑም በተቻለ መጠን ከሰው ንክኪ ማውጣት ያስፈልጋል የሚለው ትምህርት ተወስዶበታል።

ፈተናውን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ የፈተናውን አካሄድ ግልጸኝነቱ የተጠበቀ ያደርጋል፣ ውጤቱንም በእለቱ መውሰድ ያስችላል። ይህ እየተሰራበት ሲሆን እስከ ግንቦት 2015 ዓ.ም ይጠናቀቃል። በተቻለ መጠን ከሰው ንክኪ ለማውጣት ይሰራል።

ፖለቲካን ከትምህርት ማውጣት ያስፈልጋል። የዜጎችን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚወስን በመሆኑ ፖለቲካና ፈተናን መቀላቀል አይመጥንም። ኢትዮጵያ የሚሳካላት በትውልድ ነው። መሬት ውስጥ ባለው ማዕድን ሳይሆን ከመሬት በላይ ባለው ጭንቅላት ነው። አስተሳሰብ የሌለው ማሕበረሰብ ከታች ነዳጅ ቢኖረውም እንደ ሊቢያ ብትንትኑ ይወጣል፣ እንደ ኮንጎ አልማዝ ተሸክሞ በድህነት ይማቅቃል፣ የማንም መፈንጫ ይሆናል። ኢትዮጵያ ከምድር በታችም ከምድር በላይም ጸጋ አላት። የሰውን አእምሮ ማረቂያው ትምህርት ነው። የዚህ ተማሪ ብዙ አለፈ የዛኛው ወደቀ የሚለው የፌስ ቡክ ወቅታዊ ገበያ ይሆናል እንጂ አይዘልቅም።

**አዲስ ዘመን:- የትምህርት ጥራትን መጨረሻ ላይ በሚሰጥ ፈተና ማረጋገጥ አይቻልም የሚል ሃሳብ የሚያነሱ አሉ። በዚህ ላይ ምን ምላሽ አለዎት?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** በመውጫ ፈተና ሂደት ያልጠሩ ሃሳቦች አሉ። ትምህርት የጥራት ችግር ደርሶበታል ሲባል ቁንጽል አይደለም። የችግሩ ምንጭም፣ መፍትሄውም ቁንጽል አይደለም። ችግሩን በአጠቃላይ ማየት ያስፈልጋል። ይህ መፍትሄውን ምሉዕ እንዲሆን ያደርገዋል። ችግሩን በትክክል መረዳት ካልተቻለ ምሉዕ መፍትሄ ሊገኝ አይችልም።

ተማሪ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የተቀላቀለው የሁለተኛ ደረጃ ተፈትኖ፣ ተወዳድሮ፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባውን ነጥብ አሟልቶ ነው። አንድ ተማሪ ተፈትኖ ስለገባ ችግር የለውም ጥራት አለው ተብሎ መተው አይቻልም። በየጊዜው ያለው በግብዓት ደረጃ፣ በሂደትም ውስጥ ውጤቱ ላይ ጥራትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። መግቢያው ላይ በተቻለ መጠን ፈተናው መዛኝ ነው። ጥራት ያለው ፈተና ተዘጋጅቶ፣ በፍትሃዊነት ፈተናው ተስተዳድሮ፣ በትክክል ታርሞ ተማሪዎች በፍትሃዊነት ተወዳድረው የሚገቡበት የከፍተኛ ትምህርት ስርዓት ሊኖር ይገባል።

ተማሪው ወደ ዩኒቨርሲቲው ከገባ በኋላ በየጊዜው ራሱን የሚያበቃበትን ስርዓት መገንባት ይኖርበታል። የትምህርት ተቋማትንም መልሶ መፈተሽ ያስፈልጋል። የትምህርት ተቋማትን ባለፉት 25 ዓመታት ነው ከሞላ ጎደል ያስፋፋናቸው። በርካታ ተቋማት ፈጥረናል። በሩብ ምዕተ ዓመት ውስጥ በዚህ ያህል የከፍተኛ ትምህርት ያስፋፋች አገር የለችም። ይሄ የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይዞት የመጣው ጠባሳ ደግሞ አለ። ተቋማቱ በውስጥ አደረጃጀታቸው ብቃት ሳይኖር ፣ መምህራኖችና አሰራሮቹ ሳይሟሉ እያስተማሩ ቆይተዋል። በመሆኑም ይህንን ቆም ብሎ መፈተሽ ያስፈልጋል። ውስጣዊ የሆነ የተቋማትን የአሰራር ብቃት ማሳደግ ይገባል።

ለዚህ ብዙ ጥናትና ምርምር የሚያስፈልገው አይደለም። ተቋማቱ እንዲበለጽጉና እንዲጎለብቱ ከተፈለገ የውስጥ አደረጃጀታቸው እንዲያድግ፣ ጥራት እንዲጠበቅ ከተፈለገ ጥያቄው ሄዶ የሃብት ጥያቄ ይሆናል። ሃብት ለማግኘት ደግሞ ብቸኛው ምንጭ መንግስት ነው። መንግስት በየአምስት ዓመቱ በጀት እያሳደገ ዩኒቨርሲቲዎችን ቁጥር እየጨመረ መሄድ አይችልም። በመሆኑም በመንግስት የተወሰደው ትልቁ ውሳኔ በዚህኛው ዘመን ዩኒቨርሲቲ እንዳይስፋፋ ነው። ሆኖም ያሉትን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ብቃታቸውን ማሳደግ፣ የውስጥ አደረጃጀታቸው ላይ የትምህርት ጥራትን የሚያረጋግጥ የውስጥ ብቃት እንዲኖራቸው ፤የመምህራን አቅም ማሳደግ ላይ እንሰራለን። አዳዲስ ተቋማትን ፈጥረን በብቃት ያልተዘጋጁ መምህራኖችን ቁጥር፣ የትምህርት ደረጃቸውንና የመመራመር አቅማቸውን ማሳደግ ላይ ትኩረት ይደረጋል። መምህራንን በተለያዩ አማራጮች በስራ ላይ ሆነው፣ በረጅም ጊዜ ስልጠና የመጀመሪያ ዲግሪ ይዘው ያሉ መምህራን ወደ ሁለተኛ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ ይዘው ያሉትን ደግሞ ወደ ሶስተኛ ዲግሪ እንዲያሳድጉ ይደረጋል። በስራ ላይ ያሉትን ደግሞ የተለያዩ የማስተማር ሥነ ዘዴዎችና ክህሎት ስልጠና እንዲወስዱ ለማድረግ እየተሰራ ነው።

ይሄ ግን መጨረሻ ላይ ወደሚፈለገው ደረጃ እየወሰደ፣ ያስገባነውን የሰው ሃይል በማብቃት በተቀመጠው እቅድ መሰረት የምሩቃን ገጽታ በሚባለው መሰረት በማዘጋጀት ወደ ኢኮኖሚ በመመለስ ማሕበረሰብ እየወጣ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ማረጋገጫው አንደኛው መንገድ የመውጫ ፈተና ቢሆንም ብቸኛው ሆኖ ጥራት ሊያመጣ አይችልም። መግቢያ ላይ በውድድር የገባ፣ በተቋማቱና በመምህራን ብቃት፣ በአሰራር ስርዓታቸው፣ በአመራር ብቃታቸው የጎለበቱ ተቋማትን በመፍጠር መውጫ ላይ ደግሞ ተማሪው ተረጋግጦ መውጣት አለበት። በትምህርት ጥራት ላይ የደረሰው ስብራት ሰፊ ስለሆነ በአንድ ጉዳይ ብቻ መፍትሄ ማምጣት ስለማይቻል ሁሉንም ማካተት አለብን።

**አዲስ ዘመን :- የመጀመሪያ ዲግሪ ቆይታ ዘመን ለምን በአንድ አመት እንዲጨምር ተደረገ?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** ባለፉት ጥቂት ዓመታት በፍኖተ ካርታው ምክረ ሃሳብ መሰረት የመጀመሪያ ዲግሪ ቆይታ ዘመን ከሶስት ዓመት ወደ አራት ዓመታት እንዲያድግ ተደርጓል። ተማሪዎች አንድ ዓመት በመጀመሪያ አመት



ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

ተማሪ መርሃ ግብር ተዘጋጅተው በቅተው የትምህርት መርሃ ግብራቸውን እንዲመርጡ ለማድረግ ነው። ሂደቱ ቀጥታ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ገብተው ከሚጀምሩ ይልቅ በመጀመሪያ አመት መርሃ ግብር ወስደው የከፍተኛ ትምህርት አውድና ማዕቀፍ ምን እንደሚመስል ተገንዝበው የሚፈልጉትን፣ መክሊታቸውንና አቅማቸውን ለይተው ማሳካት የሚችሉትን የትምህርት መርሃ ግብር መረጃ በማግኘት በሚመጥናቸውን የትምህርት መርሃ ግብር እንዲገቡ ያስችላቸዋል።

ትግበራው ለትምህርት መርሃ ግብሩ ያዘጋጃቸዋል። ህክምና፣ ኢንጂነሪንግም ሆነ ሌሎች ዘርፎች የሚገቡ ተማሪዎች አንድ ዓመት የማሰቢያ፣ የማስላሰያና የከፍተኛ ትምህርት ተቋምን አውድ የመለማመጃና አጠቃላይ የግንዛቤ መፍጠሪያ ትምህርቶችን መውሰድ እንደሚገባቸው ታምኖ አንድ ዓመት ተጨምሯል።

ከዚህ በተጨማሪም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተልዕኮና በትኩረት እንዲለዩ ተደርጓል። በሂደት በምርምር ዩኒቨርሲቲ፣ አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች እና አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች ሆነው አንዱ ዩኒቨርሲቲ በትኩረት በአንድ ዘርፍ የላቀ ሆኖ ይወጣል። አንዱ ማዕድን ዘርፍ ሌላው ግብርና ላይ ሊሆን ይችላል። ከእዚህ ለውጥ ጋር ተያይዞ ጥራት ላይ መስራት አሁንም ዋናው ገዢ አጀንዳ ነው። የተቋማትንና የመምህራንን አቅም ማሳደግ፣ የሚቀላቀሉትን ተማሪዎች አቅም የተሻለ ማድረግና ሲወጡም ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን :- በየዓመቱ የሚወጡ ተማሪዎችን የመመዘን አቅምና በመንግስት የምዘና ሂደት የመቀጠሉ ሁኔታ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** የመውጫ ፈተና የሚሰጠው በመጀመሪያ ዲግሪ ላይ ብቻ ነው። በዓለም ተሞክሮም በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ አይሰጥም። አገራዊ ፖሊሲ እንደመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ2015 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ በመጀመሪያ ዲግሪ በግልም ሆነ በመንግስት የትምህርት ተቋማት የሚማር ተመርቆ ዲግሪውን የሚያገኘውና ወደስራ ዓለም የሚቀላቀለው የመውጫ ፈተና ወስዶ ነው።

የመውጫ ፈተናው የሙያ ማሕበራት ሲያድጉ፣ አቅማቸው ሲጎለብት ራሳቸው የሙያ ማሕበራቱ ጠንክረው ለሙያቸው ተቆርቋሪ መሆን ሲጀምሩ ወደ ስራ ለመቀላቀል የሙያ ፈተና ይሰጣሉ። አሁን ግን በእዛ ልክ የቆሙ የሙያ ማሕበራት የሉንም። ወደ ሙያ ማህበራት ለመምጣት ለምሳሌ የህግ ስራን ለመስራት የሚያስችል ፈቃድ የሚሰጡ ማሕበራት የሉም። የኢትዮጵያ ጠበቆች ማሕበር ምዘና ሊሰጡ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሃኪሞች ማሕበርም ሃኪም ከመባሉ በፊት መሟላት የሚገባውን ምዘና ያስቀምጣል። ይህ በአጭር ጊዜ ወይንም በመካከለኛ ጊዜ ሊሆን ይችላል። በሂደት ግን የሙያ ማሕበራት ሲጠነከሩ የመውጫ ፈተና ስራን ከመንግስት ላይ ይወስዳሉ።

ፈተናው ብቻውን መፍትሄ ያመጣል ብለንም አናስብም። ተቋማቱ ካልሰሩ፣ ተማሪዎቹ ካልተጉና ካልተዘጋጁ ያስቸግራል። ተማሪዎች የሚዘጋጁት ለፈተና ሳይሆን ብቁ ሆነው መውጣታቸውን ግብ አድርገው ሲዘጋጁ ነው። የተሻለ ዜጋ ለመሆን፣ በብቃት ለመምራትና ለአገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ለማበርከት አቅም መገንባት እንደሚያስፈልግ ማመን ይገባቸዋል። ተማሪዎች ለዚህ ውጤት በእያንዳንዱ ሰዓትና የትምህርት አይነትና ዘመኑ የሚጠይቀውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ገንብቶ መውጣት ይጠበቅባቸዋል። ቢያንስ ቢያንስ ተቋማት የሚያስመርቋቸውን ተማሪዎች ማረጋገጫ ለመስጠት የመውጫ ፈተናው ያስፈልጋል።

ከገበያውም አንጻር ሲታይ ሁሉም ዲግሪ አንድ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

አይነት ሆኖ አይታሰብም። ራሱ የሚማረው፣ የቤት ስራው እየተሰራለት የሚመረቀውም ባለዲግሪ ነው። ባለዲግሪ ዋጋው አይታወቅም። ገበያው የሚለይበት አካሄድ የለውም። ዲግሪ በያዙ ተመራቂዎች መካከል በብቃት ሙያውን አሟልቶ የተመረቀው የትኛው እንደሆነ ማረጋገጫ የለም። ተቋማቱ እንደሚታዩት 72 ዓመታት ከቆየው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገና ሶስትና አራት ዓመታት ያስቆጠሩ፣ እንደአሸን የፈሉ የትምህርት ተቋማት አሉ። በእነዚህ ሁሉ ዲግሪ ይሰጣል። ዲግሪው ሲሰጥ ተማሪው የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለማሟላቱ፣ የተባለውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ስለመጨበጡ ፈትሾ ማውጣት ተገቢ ነው። ካልሆነ ግን ቀጣሪው፣ ማሕበረሰብ ይቸገራል፤ ዲግሪም ዋጋውን ያጣል። አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ይጎዳል፣ በኢኮኖሚው ኢ- ፍትሃዊነት እንዲነግስ መፍቀድ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን:- ተማሪዎች ሲገቡ እንጂ ለምን መውጫ ላይ ይፈተናሉ?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** ይሄ የብዙዎች ጥያቄ ነው፤ክርክርም ያስነሳል። እንደሚታወቀው ወደ ዩኒቨርሲቲ እያስገባን ያለው መግቢያ ላይ እየፈተንን ነው። የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈትነን 50 እና በላይ ያመጣ ነው የሚገባው። ይህንን ያላሟላ ወደ ዩኒቨርሲቲ አይሄድም።

መግቢያ ላይ ተፈትነዋል። ነገር ግን መግቢያ ላይ የተፈተነ በሙሉ ብቁ ነው ማለት አይደለም። በዲግሪ የተመረቀ ኢንጂነር እንደ ኢንጂነር ለመስራት እውቀት፣ ክህሎት፣ ችሎታ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። መግቢያ ላይ የተፈተኑት ሁለተኛ ደረጃን አጠናቅቀዋል፣ ዩኒቨርሲቲ መማር ይችላሉ የሚል ማረጋገጫ ነው እንጂ ዩኒቨርሲቲ ተምሮ ብቁ ሆኗል የሚለውን አይገልጽም።

ሌላው መምታታት ያለው ተቋማቱ በየጊዜው እየፈተኑ ውጤት እየሰጡ ያሳለፉትን ለምን መውጫ ፈተና ይሰጣል? የሚል ነው። በመንግስት 50 ተቋማት በግል ደግሞ 350 ተቋማት ቢኖሩ 400 ተቋማት በተመሳሳይ መስፈርት እየሰሩ መሆናቸውን ግምት መውሰድ ያስፈልጋል። ሁለተኛ ደረጃ በተመሳሳይ አስተምረው ሁሉም ትምህርት ቤት ወደዩኒቨርሲቲ አይላኩም፤ ሁሉንም ተማሪዎች ማሳለፍ አይቻልም።

በሁለተኛ ደረጃ ብንመለከት ከአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምንም የማያልፉበት ትምህርት ቤቶች አሉ፣ ሙሉም የሚያልፉበትም አሉ። በተመሳሳይ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲኬድ ከፍተኛ ውጤት ስላገኘ፣ ተቋሙም በየጊዜው መዝኜዋለሁ ብሎ ስላሳለፈው ከዓመት ዓመት ተላልፏል ተብሎ ስለደረሰ ብቁ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አይኖርም። ስለዚህ በግልም ሆነ በመንግስት፣ በአዲስም ሆነ በነባር ተቋም የተማረ ዲግሪ የያዘ ሰው መጨበጥ ያለበትን እውቀት መያዙን ለማረጋገጥ ይፈተናል።

**አዲስ ዘመን:- አንዳንድ ተቋማት አዲስ እንደመሆናቸው አስፈላጊ የትምህርት ግብአት አለመሟላትና መሰል ችግሮች እያሉ የመውጫ ፈተና ለመፈተን ጊዜው ነው ?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** አንዳንድ ተቋማቱ አዲስ መሆናቸው፣ መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው መሆኑ፣ የመምህራን ብቃት ማነስ፣ ብቁ ቤተ ሙከራ አለመኖር፣ መጻህፍት አለመሟላት ስላለ አሁን መፈተን ጊዜው አይደለም የሚልም ክርክር ይነሳል። የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች አቅማቸው መቼ ተመሳሳይ ይሆናል? በጊዜ ዘመን መገመት አይቻልም። በታሪካቸው ምክንያት አቅማቸው ይለያያል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 72 ዓመታት አቅም ገንብቷል። እዛ ብቁ መምህራን ሊኖሩ ይችላሉ። እዛ ያሉትን ከሌላ አንድ ዩኒቨርሲቲ ጋር እኩል እስኪሆን እንጠብቅ ስንል የአለም ፍጻሜ ሊደርስ ይችላል። ሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ አይነት አቅም የላቸውም። ነገር ግን የሁሉም ተማሪዎች ይፈተናሉ። በተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲው አቅሙ ምንም አይነት ይሁን አነስተኛው የመጀመሪያ ዲግሪ አቅም፣ እውቀትና ክህሎት ሁኔታ ስለመሟላቱ ተረጋግጦ ይሰጣል።

**አዲስ ዘመን:- ተማሪውን አስተምሮ፣ ፈትኖ ብቁ ስለሆኑ ከነሙሉ ክብሩና ጥቅሙ የሚሰጡት ዩኒቨርሲቲዎቹ መሆናቸው በአዋጅ ተቀምጦ ሳለ የዩኒቨርሲቲዎቹን ስልጣን በመመሪያ መንጠቁ ተገቢ ነው?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** የተቋማትና የሚኒስትር መስሪያ ቤት ስልጣን ልዩነት ላይ ተደጋግሞ የሚነሳ ነው። ፈተና መስጠት፣ ዲግሪ መስጠት የተቋማት ሃላፊነት ነው ትክክል ነው። ሪፎርምና ፖሊሲ መምራት ግን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሃላፊነት ነው። ሪፎርም የሚመራው በአገር ደረጃ ነው። ትግበራው የትምህርት ጥራትን ለማምጣት የመጀመሪያው ሪፎርም ነው።

የሕግ መውጫ ፈተና እየተሰራ ያለው በሕግ ፍትህ ማሻሻያ ሪፎርም ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን ነው። ሪፎርም ሁል ጊዜም መንግስት ነው የሚመራው።

የመውጫ ፈተና ሕጋዊ መሰረት የለውም በሚል ለሚነሳው 2011 ዓ.ም የወጣው የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 1152/2011 የመውጫ ፈተና ሊሰጥ እንደሚችል በግልጽ አስቀምጧል። የሕግ መሰረት አለው የሪፎርም አካልም ነው። የሪፎም አጀንዳን መንግስት የሚመራው እንደመሆኑ ሂደቱን ትምህርት ሚኒስቴር መንግስትን ወክሎ መስራቱ የስልጣን ሽሚያም ፣ መጣረስም የለውም።

የመጨረሻ ግቡ ዲግሪ የሚሰጠው ሰው አስፈላጊው እውቀትና ክህሎት ስለመላበሱ መሟላት የሚገባቸውን ትምህርት ሚኒስቴር ያስቀምጣል። ሁሉም ተቋማት ፈትነው ይስጡ ቢባሉ 400 አይነት መውጫ ፈተና ይኖራል። በመሆኑም ሁሉንም የሚለካ አንድ አይነት ፈተና ይዘጋጃል ያለፉት ዲግሪውን ያገኛሉ። ያላለፉ ተጨማሪ በርካታ እድሎች ስለሚኖሯቸው ብቁ ሆነው ሲገኙ ዲግሪውን ያገኛሉ።

በህጉ ረቂቅ ላይ ስንነጋገር የመውጫ ፈተና ሁለት ጊዜ ሞክሮ ያላለፈ የመውጫ ፈተናም እንዳይሰጥ ዲግሪም እንዳያገኝ ከልካይ ነበር። ነገር ግን ለሚበቃ ሰው ዕድል መገደብ የለበትም የሚል ስምምነት ላይ ተደርሷል። የቻለውን ያህል ይውሰድ ወጪ አሸፋፈን ላይ ዝርዝር ነገሮች ሊወሰኑ ይችላሉ እንጂ ብቁ ነኝ ባለ ጊዜ እንዲፈተን ማዘጋጀት ተገቢ ይሆናል ። ዕድል ሰጥቶ ብቁ የሚሆኑበት ዕድል አለ። ለፈተና ዝግጅት፣ ለእርማት ብዙ ወጪ አለ። ነገር ግን አሁን በትምህርት ጥራት ከደረሰው በላይ ዋጋ አያስከፍልምና ይህንን ዋጋ ችሎ መሄድ ያስፈልጋል።

አዲስ ዘመን:- አካሄዱ ብልሹ አሰራር እንዲሰፍን አያደርግም፣ በየዓመቱ ተመርቆ የሚወጣውን የሰው ሃይል ለመፈተን የሚያስችል አቅምስ አለ?

ዶክተር ሳሙኤል:- የማለፍ ምጣኔው ዝቅ የሚል ከሆነ ለብልሹ አሰራር ያጋልጣል የሚል ስጋት ይነሳል። ብልሹ አሰራር በየትኛውም አሰራር ሊፈጠር ይችላል። ቀበሌ ሄጄ መታወቂያ ማግኘት መደበኛ ስራ ነው፣ ሙብትም ነው። መታወቂያ ለማግኘት ላለማግኘት ብልሹ አሰራር አይታሰብም። መውጫ ፈተናም መደበኛ ስራ ሆኖ በሞራል በህግ ካልተመራ ብልሹ አሰራር ሊፈጠር ይችላል። ይህንን አውቆ መዘጋጀት፣ በቴክኖሎጂ መደገፍ እንዲሁም እርማቱን በተቻለ መጠን ከሰው ንክኪ ማውጣት ያስፈልጋል።

ፈተናው የሚዘጋጅበት፣ የሚያዝበትና የሚሰራጭበት ስርዓትም በተቻለ መጠን ከሰው ንክኪ ነጻ ማድረግ ይገባል። ስለዚህ የ2014 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ ፈተና የምንሰጥበት ስርዓት ትምህርት ይሆናል። በ2015 ፈተና ለመስጠት በሚደረገው ዝግጅት ቴክኖሎጂን ጨምሮ አቅም ይሰጠናል። የመጀመሪያ ዲግሪ የሚመረቁትን በዓመት ከ150 እስከ 180 ሺ ይደርሳል። ይህንን ቁጥር ማስተናገድ የሚችል የፈተና ቦታ፣ የቴክኖሎጂ ግብዓት ከባድ ነው ብለን አናስብም።

አምና የሁለተኛ ደረጃን እስከ 600 ሺህ ፈትነናል፣ መስከረም ላይ እስከ አንድ ሚሊየን የሚደርስ የሁለተኛ ደረጃን ተማሪ እንፈትናለን ብለን እናስባለን። ስለዚህ ለመፈተን የሚያቅትና የሚያስቸግር አይሆንም። ቴክኖሎጂን ካስገባን፣ ሰውን ማብቃት ለሰውየው የእድሜ ልክ ፍቱን መድሃኒት ነው። የመጀመሪያ ዲግሪ ላይ በደንብ መስራት ለእድሜ ልክ ስኬት በጣም ወሳኝ ነው።

በእውቀት የሚመራ ኢኮኖሚ መምጣቱ አይቀርም። በአቋራጭ፣ በሌብነት ሳይሆን በአቅሙ በእውቀቱ የሚኖርባት እኩል ኢትዮጵያ መገንባቷ አይቀርም። ያኔ ወሳኝ የሚሆነው የያዘው አቅምና እውቀት ነው። አብዛኛው መምህር ኑሮ ከብዶት እያለ ተማሪውን ለማብቃት ይለፋል። በራስ መተማመን የሚያስተምር መምህርም መፍጠር ያስፈልጋል። ይሄ ከሌለ ሳምንት አስተምሮ ውጤት የሚሰጠውም፣ 16 ሣምንታት አስተምሮ ውጤት የሚለካውም እኩል መምህር ይባላል። አንድ ሳምንት ባስተማረው መምህር ምክንያት ዘመኑን ሙሉ የሚያስተምረው መምህር ስም ይጎድፋል። ይሄንንን ማረም ያስፈልጋል። ተቋማት ሁሉም ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ የሚል ስም አንጠልጥለዋል። አሁን ይለያል። የመውጫ ፈተናው በመንግስትም በግል ኮሌጆችም የትኞቹ የትምህርት ክፍሎች እንደሚዘልቁ ወደፊት ገበያው ይነግረናል።

ተማሪ የማያበቃ፣ ስለከፈልኩ ብቻ ብሎ አይቀጥልም። ትርፍ ብቻ ዋና ማዕከላቸው የሆነበት ኮሌጅ ገንዘቡን አጥፍቶ፣ ሕይወቱን አበላሽቶ አይቆይም። ገበያው ራሱን እያጠራ ይመጣል። ሂደቱ የስርዓት ግንባታ አካል ይሆናል። በውድድር በፍትሃዊነት ብቻ ብቁ የሚሆንበት ነው።



የመውጫ ፈተናን እንደአንድ ሪፎርም ይዘነዋል። የፕሮግራም አከፋፈት፣ መምህራን ቅጥር፣ ተቋማት ግምገማ፣ ተቋማት ማብቃት፣ ስርዓተ ትምህርት ላይ የተወሰዱ ሪፎርሞች አሉ። ዩኒቨርሲቲዎቹን በተልዕኮና በትኩረት የመለየት ስራዎች አሉ። እነዚህ ድምር ተግባራት ይከናወናሉ። ችግሩ ቁንጽል ስለሆነ መፍትሄውም ምሉዕ መሆን አለበት። ትምህርት ጥራትን ማሻሻል የሚቻለው እነዚህ ተደምረው ነው። ታች ላይ መሰራት አለበት። ዩኒቨርሲቲ ከተገባ በኋላም ብዙ ስራ ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን:- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ለይቶ ራስ ገዝ እንዲሆን ውሳኔ ላይ የተደረሰበት ምክንያት ምንድን ነው፣ ምንስ ይጠቅማል ?**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** ትምህርት ተቋማት በራሳቸው ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ነጻነት ወሳኝ ነው። ይሄ ማለት ተጠያቂት የሌለበት፣ ከመንግስት ምንም ድጋፍ የማይደረግላቸው ማለት አይደለም። ሃብትን በማስተዳደር፣ የራሳቸውን የወደፊት አቅጣጫ የመወሰን ጉዳይ ላይ ነጻነት ሊኖራቸው ይገባል። ትግበራው ለትምህርት ጥራት፣ የትብብር እና የፉክክር መንፈስ ለማምጣት ያግዛል። በሂደትም ልሕቀትን ለማረጋገጥ በዚህ ምክንያትም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲን ለማምጣት ይረዳል።

የትምህርት ተቋማት ፕሮፌሰሮች፣ ዶክተሮች ያሉበት ነው። ሚኒስትር ዴኤታ የሚባሉ ካድሬዎች ብቻ እየመሯቸው አገር የሚያሻግር ትልቅ ነገር መፈጸም አይችሉም። ስለዚህ በአገራዊ ፖሊሲው የሚጓዙበት ያደርጋል። ራስ ገዝ ተቋማትን መፍጠር ያስፈልጋል። ይህ የመጨረሻ ግቡ ለትምህርት ጥራት ይጠቅማል። ነጻ ተቋማት ሲፈጠሩ የከፍተኛ ትምህርት ተፈትነው ውጤት ይዘው ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡትን እንደገና ፈትነው ይቀበላሉ።

የመምህራኖቻቸው የተሻለ የደመወዝ ክፍያና ጥቅማ ጥቅም አሟልተው ይቀጥራሉ። ለሚቀጥሯቸው እንደአቅማቸው ይከፍላሉ። የምርምር፣ የማሕበረሰብ አገልግሎት፣ የማስተማር፣ የጥናት ጽሁፎችን በማዘጋጀት ከውጭ በሚያስገኙት ሃብት መሰረት አድርገው ይከፍላሉ። ሂደቱ በትምህርት ጥራት ላይም አይነተኛ ለውጥ ያመጣል። አሰራሩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብቻ የሚተገበር አይደለም።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደርግ ከንጉሱ ሲረከበው ባጋጣሚ ነጻ ተቋም ነበር። የሚመሩትን ፕሬዚዳንቶቹን የሚመርጥ ተቋም ነበር። ንጉሱ ካልፈቀዱ ፖሊስ ወደ ጊቢው ለመግባት አይችልም ነበር። 1969 ዓ.ም ደርግ ስልጣን ከያዘ ጥቂት ዓመታት በኋላ የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን የሚል አዋጅ ወጥቶ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኮሚሽኑ ስር ገባ። መሪውን የሚወስነው መንግስት ሆነ። አሁን ወደነበረበት ልምዱ ሲመለስ ሰፊ ትምህርት ይወሰድበታል። በቀድሞው ነጻነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሩ ፕሮፌሰሮች ጡረታ የወጡም አሁንም ያሉትን በመጠቀም እስከ መስከረም 2015 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲውን ነጻ ብናደርገው ልምዱን ወስደን ወደሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች እናሰፋለን። በቀጣይ ሁለት ዓመታት እስከ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሆነው እንዲወጡ መንግስት አቅጣጫ አስቀምጧል።

ትግበራው የውድድርንም የትብብርንም መንፈስ ይፈጥራል። በአገር ደረጃ በተቋማት መካከል መተባበርና መወዳደር ያስፈልጋቸዋል። ተወዳድረው ከውጭም ሃብት ያገኛሉ። ከአገር ውስጥም ከንግዱም ማህበረሰብ በምርምር፣ በማማከር ገቢ ያገኛሉ። ብቁ ተማሪ ስለሚያወጡ ከመንግስትም ተጨማሪ በጀት ያገኛሉ። ውድድሩ ልህቀት ያመጣል። የትምህርት ልሕቀት በአገር ውስጥ አይገደብም። በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ተቋም መፍጠር ይገባል።

በኢትዮጵያ 70 ዓመት የቆየ ዩኒቨርሲቲ ይዘን በአለም ደረጃ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች 100 የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያለነው 10 አይሞሉም። በአለም ላይ ሶስት ሺህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያለን ተቋም በጣም ውስን ነው። በመሆኑም አለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ ተቋም መፍጠር አለብን። ዩኒቨርሲቲን በሰፈር አጥረነው መቀጠል የለብንም። ዩኒቨርሲቲ አለም አቀፍ እና ተለያይነት ያለው በመሆኑም ራስ ገዝነት በጣም ወሳኝ ነው።

**አዲስ ዘመን:- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ!**

**ዶክተር ሳሙኤል:-** እኔም ለተሰጠኝ ዕድል ከልብ አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ነፃ የንግድ ቀጠና - ለኢንቨስትመንት እድገት ተጨማሪ አቅም

**አንተነህ ቸሬ**

ሀገራት የወጪና ገቢ ንግዳቸውን ለማቀላጠፍና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰታቸውን ለማሳደግ ብሎም አጠቃላይ ምጣኔ ሀብታዊ እድገታቸውን ለማሻሻል ከሚተገብሯቸው አሰራሮች መካከል አንዱ ነፃ የንግድ ቀጠናዎችን (Free Trade Zones) ማቋቋም ነው።

ነፃ የንግድ ቀጠና «ልዩ የኢኮኖሚ ቀጠና» (Special Economic Zones) የሚባሉት የንግድና ኢንቨስትመንት መከወኛ ስፍራዎች አካል ናቸው፤ ቀጠናው እሴት የሚጨምሩ የምርት፣ የሎጅስቲክስ፣ የፋይናንስ አቅርቦትና መሰል ተግባራትና አገልግሎቶች የሚከናወንበት ቦታ ነው። በዚህ ስፍራ ምርቶችን ከማምረት በተጨማሪ አስመጪና ላኪዎች ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ በማምጣት በቀጠናው ውስጥ የሚያከማቹበት፣ የሚያቀነባብሩበት እንዲሁም መልሰው ለውጭ ገበያዎች የሚያቀርቡበት እንዲሁም ሒደቱን ለማሳለጥ ቀልጣፋ የሆነ የሎጂስቲክስ አገልግሎት የሚቀርብበትም፣ የተቀናጁ የፋይናንስና የምክር አገልግሎቶችም የሚሰጡበት ነው።

ነፃ የንግድ ቀጠና ኢንቨስትመንትን የሚጨምር፣ አዳዲስ የሥራ ዕድሎች ለመፍጠር የሚያግዝ፣ ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን የሚቀንስ አማራጭ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ቀጠና የንግድ እንቅፋቶች የሌሉበት እንዲሁም ቀረጥና ግብር ያነሰበት የንግድና ኢንቨስትመንት ማሳለጫ አካባቢ እንደሆነም ይገለፃል። በነፃ የንግድ ቀጣናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ህጋዊ አሰራሮች በሌሎቹ አካባቢዎች ከሚተገበሩት ጋር ሲነፃፀሩ የላሉና አንፃራዊ ነፃነትን የሚያጎናጽፉ ናቸው።

ነፃ የንግድ ቀጠናዎች የሚፈጥሩትን የስራ እድል፣ ለአገር በቀል የሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪው መስፋፋት የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና የባለሙያዎችንና የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ እና ለዋጋ ግሽበት መቀነስ የሚኖራቸውን ወሳኝ ሚና፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድን ለማቀላጠፍ ያላቸውን አበርክቶ በአጠቃላይ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት መሻሻል የሚኖራቸውን ጉልህ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነፃ የንግድ ቀጠናዎችን ያቋቁማሉ፤ ያስፋፋሉ።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በዓለም ላይ ከአምስት ሺ በላይ ነፃ የንግድ ቀጠናዎች አሉ። በርካታ ሀገራት ነፃ የንግድ ቀጠና ያላቸው ሲሆን፣ ለእዚህም የኢትዮጵያ ጎረቤቶች የሆኑት ጅቡቲ፣ ኬንያ፣ ሱዳን ተጠቃሽ ናቸው። ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የበለፀጉት ሀገራትም ይህን የነፃ ንግድ ቀጠና አሰራር ተግባራዊ አድርገዋል፤ እያደረጉም ነው።

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እንዲሁም መሬትን ጨምሮ ሌሎች እምቅ ሀብቶች ያላት ኢትዮጵያ ነፃ የንግድ ቀጠናን እስካሁን ድረስ ባለማቋቋሟ ማግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም ማጣቷ ተደጋግሞ ሲገለፅ ቆይቷል። የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እግር ከወርች አስረው የያዙት አንዳንዶቹ መሰናክሎች ነፃ የንግድ ቀጠናዎች በሚያስገኟቸው ጥቅሞች የሚፈቱ ናቸው።

ስለሆነም ነፃ የንግድ ቀጠና በማቋቋም የሀገሪቱን ተጠቃሚነት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ልዩ ልዩ የመሰረተ ልማትና ሕግ ማዕቀፍ ዝግጅቶች ሲደረጉ ቆይተው ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ተመርቆ ተከፍቷል። የንግድ ቀጠናው በድሬዳዋ የሚገኘውን የኢንዱስትሪ ፓርክና ደረቅ ወደብን ከዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት፣ ከባቡርና ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በማቀናጀት፣ አስፈላጊ የሆኑ የባንክና የጉምሩክ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ ወደ አገልግሎት እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል።

በነጻ የንግድ ቀጠናው ምረቃ መርሃ ግብር ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ፣ ነፃ የንግድ ቀጠና ኢትዮጵያ በእጅጉ ወደ ኋላ ከቀረችባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ እንደሆነ ተናግረዋል። ‹‹ብዙ ወደ ኋላ የቀረንባቸው ዘርፎች አሉ። ከሁሉም የበለጠ እጅግ የሚያስገርመው ነፃ የንግድ ቀጠና ሳናቋቁም እስካሁን




ድረስ መቆየታችን መተኛት ብቻም ሳይሆን በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ እንደነበርን የሚያረጋግጥ ነው። ›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ 40 እና 50 ሚሊዮን ሕዝብ በነበራት ጊዜ በነበረው አሰራር ልትቀጥል እንደማትችልም ጠቅሰው፣ ቀልጣፋ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን ማወቅና መተግበር እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል። ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የዓለም ቁንጮ የሆኑት ኃያላን ሀገራት የነፃ ኢኮኖሚ እና ነፃ የንግድ ቀጠናዎችን ምስረታ ቀደም ብለው መጀመራቸውና በዘርፉ ያከናወኗቸው ተግባራት የምጣኔ ሀብት አቅማቸውን በከፍተኛ ሁኔታ እንዳሳደገው ጠቁመዋል።

‹‹ነፃ የንግድ ቀጠና አጠቃላይ አገራዊ ምርትን፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትንና የወጪ ንግድን ለማሳደግ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። የበለፀጉት አገራት በንግድና ኢንቨስትመንት ስራቸው ትልቅ ለውጥ ያስመዘገቡት እንደ ነፃ የንግድ ቀጠና ያሉ አሰራሮችን በመዘርጋታቸው ነው። በድሬዳዋ የተቋቋመው ነፃ የንግድ ቀጠና የራሱ ሕግና አሰራር ያለው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረ ሌላ ትንሽ ኢትዮጵያ ነው›› ሲሉ አብራርተዋል።

ነፃ የንግድ ቀጠናው እንዲቋቋም የተፈለገበት ምክንያት የተቀላጠፈ የሎጂስቲክስና የንግድ ስርዓት ለመዘርጋት መሆኑን ገልፀው፤ ቀጠናውን በአግባቡ በመጠቀም በጥቅል ሀገራዊ ምርት፣ በወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፍሰት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ነፃ የንግድ ቀጠናን መመስረት የንግድ ዘርፍ ችግሮችን ለመቀነስና የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ አወንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ተዋንያን ተደጋግሞ ይገለፃል። ነፃ የንግድ ቀጠናዎች የምርትና የሎጂስቲክስ ተግባራት ተቀናጅተው በቀልጣፋ አሰራር የሚከወኑባቸው ስፍራዎች በመሆናቸው ለኢንቨስትመንት ማደግ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ። የኢንቨስትመንት እድገት የመንግስትን ብቻ ሳይሆን የባለሀብቶችን ተግባራዊ ተሳትፎና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ በመሆኑ ባለሀብቶችም ነፃ የንግድ ቀጠናው የፈጠራቸውን እድሎች መጠቀም ይገባቸዋል።

በዚህ ረገድ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ‹‹የነፃ ንግድ ቀጠና ስርዓትን እስካሁን ሳንጠቀምበት የቆየን ቢሆንም በተለይ ኢትዮጵያውያን ኢንቨስተሮች አሁን በተቋቋመው ነፃ የንግድ ቀጣና የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሊነቁ ይገባል። በዚህ ቀጠና የሚወጡ ሕጎች ከሌሎቹ ቀለል ያሉ በመሆናቸው ከፋይናንስና ከጉምሩክ ጋር የተያያዙ አሰራሮች ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆኑ ይደረጋል። ሁሉም ባለሀብቶች የተጋበዙ ቢሆንም በተለይ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች በገቢና ወጪ ንግድ ላይ እመርታ እንዲመጣና ውጤት እንዲመዘገብ ከመንግሥት ጎን ሆናችሁ መስራት ይኖርባችኋል›› በማለት ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ አሳስበዋል። የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ከሚያስመዘግባቸው ስኬቶች

**ኢንቨስትመንትን በማሳደግና ተጨማሪ የስራ እድሎችን በመፍጠር የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስ ያግዛል። የገበያ አማራጮች እንዲጨምሩ በማድረግ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲያድግም አስተዋፅኦ ያበረክታል። ይህም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ተጨማሪ አቅምና አማራጭ ይፈጥራል**

ልምድ በመቀመር በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ተጨማሪ ነፃ የንግድ ቀጣናዎች እንደሚቋቋሙም ተናግረዋል።

በነፃ የንግድ ቀጠናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ህጋዊ አሰራሮች ቀለል ያሉና ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን የሚቀንሱ በመሆናቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያደርጉትን ጥረት በአንፃራዊነት ቀላል ያደርጉላቸዋል። በነፃ የንግድ ቀጠናው ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ ድርጅቶች የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

የትራንስፖርት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና በየጊዜው እያደገ የመጣውን የአገሪቱን የገቢና ወጪ ንግድ በተፋጠነ የሎጂስቲክስ አቅርቦት ለማገዝ ነፃ የንግድ ቀጠና ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተቋቋመ እንደሆነ ገልፀዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ የልዩ ኢኮኖሚ ቀጠናዎች መስፋፋት የሀገራችንን የገቢ ጭነቶች ባጠረ የአቅርቦት ሰንሰለት በብዛት በማስገባትና ከብዛት የሚገኘው የሎጂስቲክስ ቅናሽ ለዋጋ መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተጨማሪም ተደጋጋሚ የሎጂስቲክስ ወጪዎች ለማዳን ያግዛል፤ በዚህም ይባክን የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ያስቀራል። በልዩ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች ምርቶች እሴት ተጨምሮባቸው ወደ ውጭ ሲላኩ የውጭ ንግድ ምጣኔያችንን ከማሳደግና የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ከመሆን ባሻገር የሐገር ውስጥ የምርት ግብዓት አቅራቢዎችንና መለስተኛ አምራቾችን አቅም በመጨመርና የሀገር በቀል ኢንዱስትሪዎችን በማሳደግ የገቢ ንግድን የመተካት ግባችንን ያሳካል። ከዚህ በተጨማሪም ከፍተኛ አቅም ያላቸው የውጭ ባለሀብቶችን የሚስብ በመሆኑ ሀገራችንን ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ተጠቃሚ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር አረጋ ሹመቴ እንደሚናገሩት፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው የምጣኔ ሀብት ትስስርን ለማጎልበት ይረዳል። ኢንቨስትመንትን በማሳደግና ተጨማሪ የስራ እድሎችን በመፍጠር የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስ ያግዛል። የገበያ አማራጮች እንዲጨምሩ በማድረግ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲያድግም አስተዋፅኦ ያበረክታል። ይህም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ተጨማሪ አቅምና አማራጭ ይፈጥራል።

ነፃ የንግድ ቀጠናው የሀገር በቀል ባለሀብቶች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን እንዲለምዱ እድል እንደሚፈጥርላቸው ጠቅሰው፣ ይሁን እንጂ ነፃ የንግድ ቀጠናው የባለሀብቶቹን ተወዳዳሪነት የማሳደግ ዓላማውን እንዲያሳካ ስለነፃ ንግድ ቀጠናው ለባለሀብቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ እንደሚስፈልግና ባለሀብቶችም አቅማቸውን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸውም ዶክተር አረጋ ይመክራሉ።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ በበኩላቸው፤ ‹‹ነፃ የንግድ ቀጠናው የወጪና ገቢ ንግድን ያቀላጥፋል። የወጪ ንግዱ በተፋጠነ መልኩ መከናወኑ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል ሲሉ ይገልጻሉ። የንግዱ መፋጠን የምርት ፍላጎትን ለመጨመርና ደንበኞችን ለማፍራት ያስችላል። ስለዚህ ነፃ የንግድ ቀጠና ከንግድ ልውውጥ በተጨማሪ የሀገር ውስጥና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን ለማሳደግም አወንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል›› በማለት የነፃ ንግድ ቀጠናው መቋቋም ለኢንቨስትመንት ዘርፉ እድገት የሚኖረውን በጎ ሚና ያስረዳሉ።

ነፃ የንግድ ቀጠና አዳዲስና ሰፊ የሆኑ የሥራ እድሎችን ለመፍጠር፣ ተተኪ ምርቶችን ለማምረት፣ የእውቀት ሽግግርን ለማሳደግ እንዲሁም ለአገር ውስጥ የቀረቡ ምርቶችን ለማከማቸትና የሎጀስቲክስ ወጪን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ይህም ሀገራዊ የሎጂስቲክስ ተወዳዳሪነትን ትርጉም ባለው መልኩ ሊለውጥ የሚችል በመሆኑ የሀገሪቱን የገቢና ወጪ ንግድ ስርዓት ለማቀላጠፍ ያግዛል። አሰራሩ የሚያስገኛቸው ጥቅሞችና የሚፈጥራቸው እድሎች የምርት ወጪን በመቀነስ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትም ትልቅ ሚና ይኖረዋል። እነዚህ ሁሉ ጥቅሞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለጥቅል አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ዓይነተኛ ፋይዳ አላቸው።

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ከሚሰጠው ከነፃ የንግድ ቀጠና ስርዓት ርቃ መቆየቷ ብዙ ጥቅሞችን አሳጥቷታል። የእነዚህ ጥቅሞችና እድሎች መታጣት ደግሞ በአጠቃላይ እድገቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረባት አይካድም። ስለሆነም በድሬዳዋ የተቋቋመውን ነፃ የንግድ ቀጠና በሚገባ በመጠቀምና መልካም ተሞክሮችን በመቀመርና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎችም ተጨማሪ ነፃ የንገድ ቀጠናዎችን በማቋቋም አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገቱ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያስመዘግብ ማድረግ ይገባል።

# ጎሜ

# እንደገና መወለድ

ምሕረት ሞገስ

እነተሰማ መንግስቴ የሚሰበሰቡበት መጠጥ ቤት እንደተለመደው በሰዎች ሁካታ ደምቋል። አስተናጋጆች ይሯሯጣሉ። ሰው ያለ እህል ምን ያህል? ሳይሆን ሰው በዕህል ምን እንደሚያሕል የሚታይበት ቦታ ነው። ‹‹ሰው ያለ እህል ምን ያህል?›› የሚለው አባባል በችግር እና በርሃብ ሲሰቃይ የነበረውን ብቻ ሳይሆን አሁንም ድረስ በችጋር ውስጥ ያለውን ኢትዮጵያዊ በእውነት በምግብ እጦት እንዴት እንደሚጎሳቆልና ምን እንደሚያህል በማየት ማረጋገጥ ይቻላል። በእርግጥ የእነተሰማ መንግስቴ መወፈርና ጥጋብ ሌላውን ኢትዮጵያዊ አይወክልም።

በመጠጥ ቤቱ የተሰበሰቡት ግን ገሚሱ የሚበላውን አዝዞ ሲበላ፤ ሌላው እጁን ታጥቦ ሲጠባበቅ አንዳንዶቹ አጠናቅቀው እንደተለመደው መጠጣቸውን ይዘው እየተሳሳቁ ያውካካሉ። ሁሉም ጉንጩ እና ሆዱ የተንጠለጠለ ነው። እነተሰማ መንግስቴ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩም ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ያሉ አይመስሉም። ጠግበዋል፤ ተመችቷቸዋል። እነርሱ ሰፈር የዘመኑ ችግር የለም። እንኳን ኢትዮጵያን አለምን ረስተዋል።

ዘውዴ መታፈሪያ ጎራ ያለው ዘግይቶ ነበር። ሰውነቱም አጭር እና ቅጭጭ ያለ ሲሆን፣ ጎስቋላ እና ማዲያታም ነው። ያው ወግ አይቀር ከእነተሰማ ጋር እርሱም ተሰብስቧል። የሚበላውን አላዘዘም፤ ቀጥታ የገባው ወደ መጠጡ ነው። እንደሌሎቹ ምግብ ልብላ ካለ ገንዘቡ አይበቃውም። አብሮ ለመጠጣትም ቢሆን ነገ እዛ ቦታ ላይ መገኘት አይችልም። መጠጡንም ቢሆን አንዳንድ ቀን እነተሰማ እየጋበዙት እንጂ ባያግዙት በየቀኑ ከእነርሱ ጋር መቀላቀል ይሳነው ነበር።

መብላት መፈለግ ብቻ ሳይሆን ሰውነቱ ተገቢውን ምግብ ባለማግኘቱ እያላበው ቢልፈሰፈስም ገንዘብ ስለሌለው የምግብ ዝርዝር አይጠይቅም። ምንም እንኳ እነተሰማ ቢከፍሉለትም እንኳን ምግብ አዞ ሊበላ ‹‹ሰው ያለቤቱ ያንሳል ጉልበቱ›› እንዲሉ መጠጡንም ቢሆን ተዝናንቶ እስኪበቃው አይጠጣም። ተሳቅቆ ለሱሱ ያህል ትንሽ ይጎነጫል፤ ራሱን ለመርሳት እና ወጪውን ለመቀነስ ደግሞ እንደነተሰማ ውስኪ ከመጠጣት ይልቅ በቢራው ላይ አረቄ ይደርብበታል። ከዛ ሞቅ ሲለው መደንፋት ይጀምራል። በጠገበ ሆዱ ሳይሆን በተራበ አንጀቱ መጠጥ የሞላውን ጭንቅላቱን አንገቱ መሸከም እያቃተው ጎንበስ ቀና እያለ ያለበትን ደረጃ ይረሳል። እነተሰማ መንግስቴን ይሳደባል። አንዳንዴ በስካር ሌላ ጊዜ ደግሞ የሰከረ አስመስሎ ልቡ ውስጥ ያለውን በሙሉ ዘርዝሮ ይዘከዝካል።

አንዳንዴ እነተሰማ ጓደኛቸው ዘውዴ ሞቅ ብሎትም ቢሆን የሚናገረው እውነት እንደሆነ በማመን በልዩነታቸው ይሳቀቃሉ። በተለይ ፖለቲካ ነክ ጉዳይ ላይ መነጋገር ከተጀመረ፤ ዘውዴ ልቡ ጮቤ ይረግጣል። እንደፈለገ ይዘረጥጣቸዋል። እነተሰማ ለመከላከል ይሞክራሉ፤ ነገር ግን ለእርሱ ምላሽ መስጠት ቀላል አይሆንላቸውም። ‹‹እናንተ ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም። ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያ የሚሞት እንጂ ለሆዱ የሚሞት ከርሳም በልቶ አደር አይደለም። ›› ይላቸዋል። በተለይ የአንድአንድ ቀን ንግግሩ ለመስማት ከባድ ይሆናል።

‹‹እናንተ እኮ ለኢትዮጵያ ልጆቿ ሳትሆኑ የሩቅ ባዳዎች ናችሁ። እንዲያውም ባዳ ያው ባዳ ነው። ቢያንስ ሰው ላይ ላይደርስ ይችላል። እናንተ ግን ባዳ መሆን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ እሳት እየጫራችሁ እስከ ማፋጀት የምትደርሱ የአንጀት ስር በሽታዎች ናችሁ። ሆዳችሁን መሙያ ካገኛችሁ ምንም ለማድረግ ወደ ኋላ አትሉም። እኛ እውነተኛ ልጆቿ የምንልሰው የምንቀምሰው ያጣን ምስኪን ድሃዎች ነን። ሃብታችንን መጠቀም የተከለከልን በዛም ምክንያት በረሃብ እየተቆላን ያለን ምስኪን ድሃዎች፤ በገዛ ሃብታችን ሌላው እየበላ ሲጠግብ እኛ ግን የሚበሉትን እያየን ልክ እኔ ዛሬ እንደሆንኩት እንራባለን። እኛ ርቦናል፤ ረሃባችንን እናስታግስበት ብንላቸውም እንደናንተ አይነት የውጪ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሊገባቸው አልቻለም። ሳይርበው የሚበላ ርሃብን አያውቀውም እንደሚባለው እነርሱ ተርበው አያውቁም፤ ስለዚህ የእኛ ርሃብና ችግር አይገባቸውም።

ሰው ያስገድላል አባይ፤ ውሃ ያስጮሃል ድንጋይ እንዲሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች በውሸት ይኖራሉ። በውሸት ሰው ያስገድላሉ። የኢትዮጵያ አድባር የኢትዮጵያ ሲሳይ የሆነውን አባይ መነሻው ኢትዮጵያ እንደሆነ አያምኑም። ውሸት ያወራሉ፤ ሰው ያሳስታሉ። አንድ ሰውን ብቻ ሳይሆን ትውልድን በተሳሳተ መንገድ ይነዳሉ። እንኳን መራብ ጥጋባቸው እንዲቀንስ አይፈልጉም። እናንተም ተመሳሳይ ናችሁ። እነርሱ ጠግበው ለአገራቸው ይቆማሉ። እናንተ በተቃራኒው የውስጥ የኢትዮጵያ ጠላቶች የገዛ አገራችሁን አጥንቷን ግጣችሁ ሆዳችሁን በመሙላት ፈጥናችሁ እየተራመዳችሁ የተሰጣችሁን ሃላፊነት ከመወጣት እና አገር ከመጥቀም ይልቅ ቦርጫችሁን በመከራ ትጎትታላችሁ። ሰው እና እንጨት ተሰባሪ መሆኑን አትረዱም። ከዚህ አሁን ስትወጡ ተሰብራችሁ ልትቀሩ ትችላላችሁ፤ ይህንን ማሰብም ሆነ መስማት ስለማትፈልጉ ምንም ማድረግ አይቻልም። ነገር ግን ማወቅ ያለባችሁ የነገ የታሪክ ተወቃሾች ናችሁ። ›› አለ።

አላቋረጠም ቀጠለ፤ ‹‹አሁን ኢትዮጵያን እየበደላት ያለው የውጪው ብቻ ሳይሆን ውስጧ ያለው ጨካኝ ልጇ ነው። ማንኛውም ሰው አላፊ በመሆኑ የማይሞት ሥራ በመሥራት እንደገና እንዲወለድ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈቀደበት ወቅት ቢሆንም፤ አንዳንዶች ግን በአላፊ ንዋይ ተመስጠው እና በዛም ተታልለው አገራቸውን እየጎዱ ነው። ግብፅ ‹ናይል የፈጣሪ ገፀ-በረከቴ ነው› ብላ በውሸት ለመጠቀም ስትሞክር፤ እኛ ደግሞ አባይ ከገዛ ምድራችን የሚመነጭ መነሻውን በተራራው ላይ ያደረገ የግብፅ ሳይሆን ለኢትዮጵያ የተሰጠ የፈጣሪ ስጦታ ቢሆንም ግብፅም ሆነች ሱዳን እንዲሁም ሌሎቹም የተፋሰሱ አገሮች ሊጠቀሙበት ሙብት አላቸው ብለን የራሳችንን ርሃብ ለማስታገስ ስንዳክር ነገር ግን እንደናንተ አይነት ከርስ ወዳድ መብላትም ሆነ ረሃባችንን ማስታገስ እንዳንችል እንቅፋት ሆኖብናል። ባንጠግብ እንኳ እንዳንራብ ብትፈቅዱልን ምን አለ?›› ሲል ሁሉንም በጥያቄ አፋጠጣቸው። መልስ የሰጠው አልነበረም።

ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ዋግ የመታው ስንዴ እንዲሉ እነተሰማ ሁሉም ጥጋባቸው ጠፋ፤ ድንጋጤ ተሰማቸው። አንደኛው ጓደኛቸው አዳነ ግን ለዘውዴ መልስ መስጠት ፈለገ። ‹‹በምን መስፈርት እኛ እና ግብፅ አንድ እንሆናለን? ይሔ መቼም ለምን ወፈሩ? በሚል ቅናት እንጂ ለምንበላበትም ሆነ ለምንጠጣበት ግብፅ ገንዘብ ለእኛ የምትሰጥበት ምንም አይነት መንገድ የለም። ሊኖርም አይችልም ይህንን ጠንቅቀህ ታውቃለህ። ›› አለው።

‹‹በማያገባቸው የሚገቡ ያለሃሳብ የሰው በቅሎ የሚሰቡ ጣልቃ ገቦች እየሰጡን አይደለም ብለሕ ሞግተኝ። ›› በማለት ዘውዴ አዳነ ላይ አፈጠጠ። አዳነ አልገባውም ግራ ገባው ‹‹እነርሱ ደግሞ እነማን ናቸው? ›› ሲል ጠየቀ። ዘውዴ በበኩሉ ‹‹ያው ተዘዋዋሪ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው። ›› አለና መለስ ብሎ ለነገሩ እናንተ አይገባችሁም። ገንዘቡ ኪሳችሁ ውስጥ መግባቱ እንጂ የመጣው ከየት እና እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ አያሳስባችሁም፤ ጭራሽ አይገባችሁም። ለእናንተ ማስረዳት ድንጋይ ላይ ውሃ እንደማፍሰስ ነው። ›› ሲል አዳነ በስጨት አለ። ወዲያው ራሱን ተቆጣጠረ፤ ቀጫጫው ዘውዴ ላይ እጁን መሰንዘር አልፈለገም።

አዳነ ዘውዴን የውሃ ላይ ኩበት እንደሆነ በከንቱ የሚንሳፈፍ ከመፍረስ ውጪ ተስፋ የሌለው ነው ብሎ በመገመት ‹‹ አንተን እኔ ሳልመታህ ሕይወት ራሷ መትታ ከምድር ታጠፋሃለች። ›› አለው። ዘውዴ መረር ብሎ ተናገረ፤ ‹‹እውነት ትቀጥናለች እንጂ አትበጠስም ሲባል አልሰማህም? እኔ ሁልጊዜም የምናገረው እውነት ነው። መቀበል ያለባችሁን ተቀበሉ። እንደግብፃውያን ስለአገራችሁ ቁሙ። በምልጃ እና በውንብድና ሰርታችሁ ከማግኘት ይልቅ በሃቅ ላይ ተመስርታችሁ ፍትሃዊ አገልግሎት ስጡ። ሁሉንም እኩል ካገለገላችሁ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ትሆናላችሁ። ምንም እንኳ እስከ ዛሬ ኢትዮጵያን ብታስቸግሩም፤ ብዙ ጥፋት ብታጠፉም ይቅር ትባላላችሁ። ጠግበው እያደሩ ኢትዮጵያን ከሚያስርቡ ወይም ኢትዮጵያውያን በልተው እንዳያድሩ ከሚተጉ የውጪ ጠላቶች ተለይታችሁ ትታያላችሁ። የዘመድ ጥል የሥጋ ትል እንዲሉ ብንጣላም አንለያይም ። የዘመዳም ጠብ ቂም ስለሌለው አያራርቅምና ተለያይተን አንለያይም።

ይቅር እንላችኋለን። ነገር ግን እንደግብፅ ወይም በማያገባቸው እየገቡ አሸማጋይ ለመምሰል የሚሞክሩ እና ኢትዮጵያውያንን እንዳያድጉ እንደሚተጉ ከፉ የውጪ ሰዎች አትሁኑ። እንደግብፃውያን ሁሉ ስለሃገራችሁ ትጉ፤ ለአገራችሁ ታሪክ በመስራት ዳግም ተወለዱ። የአባይ ግድብ ተጠናቆ ኢትዮጵያ ከፍ እንድትል ሃላፊነታችንን እንወጣ፤ የግብፅ ስግብግብነት በልክ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን በየሰበቡ በኢትዮጵያውያን መካከል የሚፈጠር ክፍተትን እንድትጠቀምበት አንፍቀድላት።

የአህያ ስጋ ከአልጋ ሲሉት ከአመድ እንዲሉ ያለበለዚያ ክብር የሌለው ሰው በገዛ እጁ እንደሚዋረደው ሁሉ እኛም እንዋረዳለን። የኢትዮጵያ ዕድገት የሁላችንም ዕድገት ነው። የኢትዮጵያ ጉስቁልና እና ጉዳት የሁላችንም ጉስቁልና እና ጉዳት በመሆኑ እንደራሳችን እንየው፤ እየጠገቡ የተራበን መርሳት አያዋጣም። አሁን በዚህ ዘመን ለዓባይ ግድብ የሠራ ሁሉ ዳግም እንደተወለደ ነው። ከውጪው በላይ ውስጥ አዋቂ የበለጠ የሚጎዳ በመሆኑ ከውስጥ ሆናችሁ አገራችሁን ኢትዮጵያን እንዳትጎዷት›› ሲል አጠቃለለ።

ተሰማ ግን የዘውዴ ማጠቃለያ ትንሽ ቆርቁሮታል፤ ‹‹ ውስጥ አዋቂ በመሆኑ የበለጠ የሚጎዳው ማን ነው? ለምን አንተ ሁል ጊዜ ራስህን ነፃ፣ ምንም ያላደረገ ፣ አገሩን ብቻ ሲጠቅም የኖረ ሰው ታስመስላለህ? ይህ ትክክል አይደለም። ኢትዮጵያን ጎድታችኋል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ጎድተናታል በል። ›› አለው።

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹እኔ ኢትዮጵያን አልጎዳሁም የሚል ሃሳብ አልሰነዘርኩም። ›› ሲል ተሰማ ደግሞ ‹‹እናንተ ኢትዮጵያን ጎድታችኋታል፤ ማለት እኔን አያካትትም እያልክ ነው። አንተም የእኛው አካል ስለሆንክ ኢትዮጵያን ጎድተናታል በል›› አለው።

ዘውዴ ቆም ብሎ ሁለት እጆቹን ደረቱ ላይ አድርጎ ‹‹እናንተ ብቻ አይደላችሁም፤ እኔም ኢትዮጵያን ጎድቻታለሁ። ቢያንስ ሌሎች ሲጎዷት እያየሁ ዝም ብዬ አልፌያለሁ። ስለዚህ ተጠያቂ ነኝ። እኔም ሃላፊነት አለብኝ። ነገር ግን ከአሁን በኋላ ቢያንስ የአገር ልጅ የማር እጅ እንዲሉ ወገን አገርን የሚረዳ እና በችግር ጊዜ የሚደርስ ነውና ለጎስቋላዎቹ ኢትዮጵያውያን እንድረስላቸው እላለሁ። በሉ ለዛሬ ለእኔም ድረሱልኝ የጠጣሁበትን ክፈሉልኝ›› ብሎ ሲወጣ ሁሉም አውካኩ። ዘውዴ መንገድ ሲጀምር ስካሩ ለቅቆት ነበር። ዛሬ የተበሳጨው በድህነቱ ሳይሆን በግብፅ ስግብግብነት ነው። ያንንም ለነተሰማ ስለገለፀ ደስ እያለው መንገዱን ቀጠለ።

> **በምልጃ እና በውንብድና ሰርታችሁ ከማግኘት ይልቅ በሃቅ ላይ ተመስርታችሁ ፍትሃዊ አገልግሎት ስጡ። ሁሉንም እኩል ካገለገላችሁ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ትሆናላችሁ። ምንም እንኳ እስከ ዛሬ ኢትዮጵያን ብታስቸግሩም፤ ብዙ ጥፋት ብታጠፉም ይቅር ትባላላችሁ። ጠግበው እያደሩ ኢትዮጵያን ከሚያስርቡ ወይም ኢትዮጵያውያን በልተው እንዳያድሩ ከሚተጉ የውጪ ጠላቶች ተለይታችሁ ትታያላችሁ። የዘመድ ጥል የሥጋ ትል እንዲሉ ብንጣላም አንለያይም ። የዘመዳም ጠብ ቂም ስለሌለው አያራርቅምና ተለያይተን አንለያይም**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የሮፍናን ‹‹ዓባይን የመሆን›› ህልም በዩኒቨርሳል ሪከርድስ እየተሳካ ይሆን?

ይበል ካሳ

“ሰከላ ዓባይን ወለደች፣
እናቴም እኔን”

ይህ በአንድ ጊዜ እንደሚሰማ አንድ የዘፈን ትራክ ዓይነት ቅርጽ ይዞ በተቀነባበረውና “ሦስት” ብሎ በተሰየመው (Truck liked album) አልበሙ ውስጥ ሙዚቀኛውና የድምጽ መሃንዲሱ ሮፍናን ኑሪ እየደጋገመ የሚያዜማት መሪ የዘፈን አዝማች ናት። በዚች መሪ የዘፈን አዝማች ስንኝ ውስጥ አርቲስቱ ንጽጽራዊ ዘይቤን በመጠቀም በሁለት ጥንድ ነገሮች መካከል ያለውን መመሳሰል ሊነግረን ይሞክራል። በሰከላና በእርሱ እናት፣ በዓባይና በእርሱ(በሮፍናን) መካከል አንዳች ዓይነት የባህሪይ አንድነት መኖሩን ይነግረናል። እናቱን ከሰከላ ጋር፤ ራሱን ደግሞ ከዓባይ ጋር ያነጻጽርልናል።

ታዲያ ሮፍናን ይህን ይበለን እንጂ እናቱ ከሰከላ፤ እርሱ ከዓባይ የሚመሳሰሉት በምን እንደሆነ ግን አይነግረንም፤ በእነዚህ አካላት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት እኛው ራሳችን ፈልገን እንድንደርስበት ክፍት አድርጎ ትቶልናል። ወትሮም ባለቅኔ ሃሳቡን የሰም ካባ አልብሶ፣ በምሳሌ ሸፋፍኖ፣ የልቡን ፍላጎት በቅኔ ሞሽሮ ነውና ለታዳሚ የሚድረው በፈቀደችልን ልክ ሙሽራዋን ገልጦ ማየት ለእያንዳንዳችን የተሰጠ ኃላፊነት ነው። ታዲያ በሮፍናን ቅኔ ውስጥም ከሰሙ ባሻገር ሁሉም የየራሱን ወርቅ አይቶ ይሆናል፤ እኔ ያየሁትን በዚህ ጽሁፍ ላካፍላችሁ ወደድኩ። ሰከላ ከባህር ዳር ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋና ከተማ ባህርዳር ደቡባዊ ምዕራብ 165 ኪሎ ሜትር፤ ከመዲናችን አዲስ አበባ ደግሞ 430 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ምዕራብ ጎጃም ውስጥ የምትገኝ ወረዳ ናት። ታዲያ የበርካታ ወንዞች መፍለቂያና የተለያዩ ምንጮች መገኛ ከሆነው ውኃ አዘሉና ውርጫማው የጮቄ ሰንሰለታማ ተራራዎች ሥር የምትገኘው ሰከላ ወረዳ ግሽ ዓባይ የምትባል አንዲት ቲንሽ ምንጭ አለች። ይሁን እንጅ ይች ቲንሽ ምንጭ የዓለማችን ረጅሙ ወንዝ ዓባይ ፤ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው ደግሞ ከምድር ተነስተው ገነትን ከሚያጠጡ አራት አፍላጋት መካከል ሁለተኛውና “እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል” የተባለው ታላቁ ግዮን ወንዝ መፍለቂያ ናት። የሰከላ ወረዳ ዋና ማዕከል የሆነችው የወረዳዋ ዋና ከተማ የተሰየመችውም በዚችው ምንጭ ስም ነው። እናም ሰከላ የታላቁ የዓለማችን ወንዝ ዓባይ መነሻ ስፍራ ናት። እንግዲህ ከሮፍናን እናት ጋር የተነጻጸረችው ሰከላ ከዓባይ ጋር ያላት አፍአዊ ዝምድናና “ሰከላ ዓባይን ወለደች፤ እናቴም እኔን” የሚለው የዘፋኙ ቅኔ ሰሙ ይኸው ነው። ወደወርቁ እንለፍ። በእኔ ዕይታ በዚች ቅኔያዊ መሪ የግጥም አዝማች ሊተላለፍ የተፈለገው ሚስጥራዊ መልዕክት ወይንም የቅኔው ወርቅ “መነሻህ ምንም ይሁን፣ ትንሽም ይሁን ትልቅ ቦታ መድረስ ትችላህ” የሚል ነው።

ሮፍናን “ሰከላ ዓባይን ወለደች” ካለ በኋላ “እናቴም እኔን” በማለት ሰከላና እናቱን ያመሳስላል። ሰከላ ያገሬው ሰው እንኳን በቅጡ የማያውቃት ምንም ትንሽ ወረዳ ብትሆን ከዓለማችን ወንዞች ሁሉ ረጅሙን፣ ከፈለቀበት ቀየ አልፎ ዓለም ሁሉ የሚያውቀውን፣ ዝነኛውንና ታላቁን ዓባይን ወልዳለች። እናም ሮፍናን “የእኔም እናት እንደዚሁ ከጎረቤቶቿ በቀር ብዙም የማትታወቅ፣ ያን ያህል ዝና የሌላት ሴት ብትሆንም “ታላቅና ዝነኛ የሆንኩትን(መሆን የምችለውን) እኔን ወልዳለች” የሚል መልዕክትን ለማስተላለፍ የፈለገ ይመስለኛል።



“የእኔም እናት እንደዚሁ ከጎረቤቶቿ በቀር ብዙም የማትታወቅ፣ ያን ያህል ዝና የሌላት ሴት ብትሆንም “ታላቅና ዝነኛ የሆንኩትን(መሆን የምችለውን) እኔን ወልዳለች”

ይህንንም ራሱ ከሰሞኑ ስድስት የሚል ሦስተኛ አልበሙን ካሳተመ በኋላ በሸገር ኢ.ፍ.ኤም የቅዳሜ ጨዋታ ፕሮግራም ላይ ከ ጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ ጋር በነበረው ቆይታ ገልጿታል። ሮፍናን ለእርሱ እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ የእናቱ አስተዋጽኦ እጅግ ትልቅ እንደሆነ ይናገራል። “ለእኔ ትልቅ ነገር የሚሆነኝ ከመሰላት ግን ምንም ነገር አትከለክለኝም፤ ደግሞም ትልቅ እንደምሆን እርግጠኛ ነበረች። ምንም ነገር ሞክሬ ሚያቅተኝ አይመስላትም ነበር” ይላል። ከልጅነቱ ጀምሮ የእናቱን ድምጽ እየቀረጸ የማዳመጥ ልማድ የነበረው መሆኑን የሚያስታውሰው ሙዚቀኛ ሮፍናን “...እና ዩኒቨርሳል ሪከርድስ ልናስፈርምህ እንፈልጋለን ሲለኝ መጀመሪያ ወደአዕምሮየ የመጣው ያኔ በልጅነቴ እናቴ ባወራች ቁጥር ድምጽሽን ልቅዳው ስላት እምቢ ብላኝ ቢሆንስ? የሚለው ነው። ግን እኮ ችላ አይደለም ዝም ብላ ነገር ነው የምታወራው” በማለት እናቱ እንደብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን እናቶች ዘመናዊ ዕውቀት ያልነበራቸው ሴት መሆናቸውን ይነግረናል። ይሁን እንጂ ከቲንሿ ሰከላ ፈልቆ ታላቅና በዓለም ዙሪያ ታዋቂና ዝነኛ ወንዝ መሆን እንደቻለው ዓባይ እናቱ ምንም ነገር ፈልጎ ማድረግ እንደማያቅተውና ከሁሉም በላይ እንደሆነ እንዲሰማው አድርገው ያሳደጉት ሮፍናንም ምንም እንኳን ከታዋቂና ከዝነኛ ቤተሰብ ባይወለድም አንድ ቀን ትልቅ ደረጃ ላይ እንደሚደርስና ዝናው በዓለም ሁሉ እንደሚናኝ ዕምነቱ ነበረው። ይህንንም ነው “ሰከላ ዓበይን ወለደች፣ እናቴም እኔን” በማለት ሦስት በተባለው አልበሙ ላይ በቅኔ የነገረን።

ሮፍናን በጊዜው በዚያ ደረጃ ላይ የተቀመጠ ታላቅ ሰው አለመሆኑን ባያጣውም አንድ ቀን በጊዜ ሂደት ግን ከራሱ አልፎ እናቱንና አባቱን፣ ብሎም ሃገሩን የሚያስጠራ፣ ዝናው በዓለም ሁሉ የናኘ ታላቅ ሰው መሆን እንደሚችል ውስጡ ይነግረው ነበር፣ እንደሚያሳካውም በራሱ እርግጠኛ ነበር። እነሆ “ሰው በልቡ እንዳሰበው እንዲሁ ይሆናል” ነውና ቃሉ አሁን ላይ ሮፍናን ህልሙ እውን የሚሆንበት ጊዜ ላይ የደረሰ ይመስላል። ለምን ቢሉ ድንቅ ተሰጥኦውንና ትልቅ ደረጃ ላይ የመድረስ ሕልሙና ዕምነቱን አይቶ የዓለማችን ትልቁ የሙዚቃ ኩባንያ ዩኒቨርሳል ሬከርድስ ቤቱ ድረስ መጥቶ አስፈርሞታልና!

ዩኒቨርሳል ሪከርድስ በስድሳ ሦስት የዓለም ሃገራት ትልልቅ ቅርንጫፎች ያሉት፣ የዓለምን የሙዚቃ ገበያ 98 በመቶ የተቆጣጣረ የዓለማችን ትልቁ የሙዚቃ ካምፓኒ ነው። ከሙዚቃ ንጉሡ ማይክል ጃክሰን እስከ የሙዚቃ አብዮተኛው የሬጌ ፈጣሪው ቦብ ማርሌ፣ ከማዶና እስከ ሪሃና፣ ከካንትሪ ሙዚቃ ፈርጦቹ ኬኔ ሮጀርስ እስከ ሊዮኔል ሪቸ፣ ከራፕ ንጉሱ ቱፓክ ሻኩር እስከ ኢሚኔም፣ ከካቲ ፔሪ እስከ ቢዮንሴ፣ ትልልቆቹ የዓለማችን ዝነኛ ድምጻውያን በዩኒቨርሳል ሪኮርድስ በኩል አልፈው ወደዝና ማማ የመጡ ናቸው። ከሞሮኳዊው ሻሃታ ሃሰን እስከ ደቡብ ኮሪያዊው ሱፐር ጁኒየር...ከኢንዶንዥያ እስከ አልባኒያ፣ ከደቡብ አሜሪካ እስከ ካሪቢያን እስያ... በሰባቱም አህጉራት በየሃገሩ የሚገኙ ዝነኛ አቀንቃኞችና አርቲስቶች ዝናቻው ከሃራቸው አልፎ በዓለም ዙሪያ እንዲናኝና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ያስቻላቸው ግዙፉ ዓለም አቀፋዊ የሙዚቃ ኩባንያ ዩኒቨርሳል ሪከርድስ ነው።

እናም ለአንድ አርቲስት ከዩኒቨርሳል ሪከርድስ ጋር መሥራት ማለት ከትውልድ ሃገሩ ተሻግሮ በመላው ዓለም የሚታወቅበትን ዕድል ማግኘት ማለት ነው። የሮፍናንም ህልም ይኸው ነው፤ የሙዚቃ ስራው በሃገሩ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የሚደመጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችል ዝነኛና ታላቅ አርቲስት መሆን። በሸገር ኤፍ.ኤም የቅዳሜ ጫዋታ ፕሮግራም ላይ ራሱ ሮፍናንም እንዳለው ይህን ዕድል ማግኘት ቀላል ነገር አይደለም። የሙዚቃውን ንጉስ ክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰን ጨምሮ የሃገራችን ትልልቅ ዝነኛ ድምጻውያን ያላገኙት ወርቃማ ዕድል ነውና። በዓለም አቀፍ ደረጃ መደመጥ የሚችል ሙዚቀኛና ድምጻዊ አጥተን፤ ሙዚቃችንም በዓለም አቀፍ ደረጃ የመደመጥ አቅም ስላለው ሳይሆን እንደዛ እንዲሆን የሚያስችል ሥራ ባለመሠራቱ የተነሳ በእርግጥም ለአንድ ኢትዮጵያዊ አርቲስት ይህን እንደ ትልቅ ዕድል የሚቆጠር ብቻ ሳይሆን ትልቅ ድልም ነው። እምነቷ ተራራን የሚያንቀሳቅሰው ያች ምስኪን እናቱ ምንም ነገር ማድረግ እንደማያቅተውና ከሁሉም በላይ እንደሆነ እየነገረች ያሳደገችውና ከትንሽም ሆነ ከትልቅ፣ ሰው ከየትም ይወለድ ራሱን ለትልቅ ነገር ካጨና ትልቅ ደረጃ ላይ እደርሳለሁ ብሎ ካመነ “እንደእምነቱ ይሆንለታል” ብሎ የተነሳው ብላቴናው ሮፍናን ግን አንድ ቀን ይህን ያሰበው እንደሚሳካ ቀድሞ ገብቶታል። ይህንንም “ሰከላ ዓባይን ወለደች፣ እናቴም እኔን” በማለት በሙዚቃው ተናግሮ ነበር። “አንተ መሆን የምትፈልገውን ነገር ከልብህ ወደኸው ጽኑ ፍላጎት ኖሮህ በተግባር መጣር በምትጀምርበት ጊዜ ፍላጎትህ እንዲሳካ መላው ዓለም ከአንተ ጋር አንድ ላይ ያሴራል” እንዲል የምንጊዜም ምርጥ ሽያጭ መጽሐፍ የ“ዘ አልኬሚስት” ደራሲው ፓውሎ ኩዊንልሆ ከልብ ካመኑና በርትተው ከጣሩ ሁሉ ይቻላልና እነሆ ለታላላቆች ያልተቻለው ለሮፍናን ተችሏል።

ከአፍሪካም ይሁን ከአሜሪካ፣ ቋንቋው ዓለም አቀፍም ይሁን ሃገርኛ፣ እንግሊዝኛም ይሁን አማርኛ ከልብ ካመኑና ከጣሩ ሁሉ ይቻላልና ስንት ታላላቅ የሃገራችን ድምጻውያን ያልቻሉትን በዓለም አቀፍ መድረክ የመሥራትና የመታወቅ እድል ሮፍናን ሊያገኘው ችሏል።

ባገኘው ትልቅ ዕድል እጅግ መደሰቱንም ገልጿል። እንዲህ ሲል፡- “ዩኒቨርሳል ሪከርድስ የዓለማችን ትልቁ የሙዚቃ ኩባንያ ነው፤ ይህን ዕድል ማግኘቴ ለእኔ ትልቅ እድል ነው። ጎፋ ተወልዶ ቄራ ላደገ፣ በሕዝብ ትምህርት ቤት ለተማረ፣ ለአንድ ኢትዮጵያዊ አርቲስት እዚህ ደረጃ መድረስ ቀላል አይደለም። አንድ አሜሪካዊ ይህንን ዕድል ለማግኘት ብዙ መከራውን ነው የሚያየው፤ ይህንን በሚያክል ትልቅ ዓለም አቀፍ የሙዚቃ ካምፓኒ እውቅና አግኝቼ አብሬ እንድሠራ ዕድል ማግኘቴ ለእኔ እጅግ ትልቅ ዕድል ነው። እንዲህ ዓይነቱን ዕድል ማግኘት መመረጥ ነው፤ በዚህም ኩራት ይሰማኛል”።

የሮፍናን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ወደትልቅ ደረጃ መምጣትና ከትውልድ ሃገሩ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂና ዝነኛ ሊያደርገው የሚያስችልውን ሥራ መሥራት የሚችልበትን ዕድል ማግኘት ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለሃገሩ ኢትዮጵያም ትልቅ እንድምታ ያለው መሆኑንም አርቲስቱ ተስፋውን አመላክቷል። “ሙዚቃችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ወጥቶ እንዲሰማና ዕውቅና እንዲያገኝ፣ ትልቅ ገቢ ምንጭ እንዲሆን በር የሚከፍት በመሆኑ ለእኔ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ለሃገራችንም ትልቅ ዕድል ነው ብዬ አስባለሁ። አፋን ኦሮሞ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ ሙዚቃዎችን ትልልቅ ዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ሲዘፈኑ ለመስማት፤ የወላይታ፣ የጋምቤላ...የሃገራችን ሙዚቃዎች ከእኛ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ መድረኮች ላይ ለመስማት ምናልባት እኔ በር ሆኜ ይሆን ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል” ብሏል። የሃገር ታሪክ ዜጎቿ የሚሠሩት ታሪክ ነውና በእርግጥም የሮፍናን ወደዓለም አቀፍ መድረክ የመምጣት ታሪክ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለሃገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪም የራሱን አሻራ የሚያስቀምጥ ነውና አስተዋፅኦው በቀላል ሚታይ አይደለም። እናም በአርቲስቱ ሕልም ውስጥ የእኛም የሁላችንም ሕልም አለና ሕልሙ እንዲሳካ ከልብ እንመኛለን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## እኔና ልጆቼ

**ሰላማዊት ውቤ**

ከወላጆቼ ቤት ትዳር ይዤ እንደወጣሁ ነው ያረገዝኩት። እርግዝናው አስቤበትና ፈልጌው ነው የመጣው። የአብራኬ ክፋይ የሆነ የራሴ ልጅ እንዲኖረኝም በብርቱ እመኝ ነበር። ትዳር የመሰረትኩበት የመጀመርያ ዓላማዬም ልጅ መውለድን መሰረት ማድረጉን አስታውሳለሁ። እንዳለምኩትም ልጅ መጸነሴ ተነገረኝ። ደስ አለኝ።

ተከታታይ የወሊድ ክትትል ለማድረግ ለመጀመርያ የሄድኩት ካዛንቺስ ጤና ጣቢያ ነበር። እናት ልሆን በመሆኑ ልቤ በደረቴ ተፈጥርቆ እስኪወጣ ደስ ብሎኝ እንደነበርም አልዘነጋውም። ክትትሉን ለመጀመር የሚያስችለው ቅድመ ምርመራ ሲደረግልኝ ሁሉ ሁለመናዬ ጥርስ በጥርስ ነበር። ሆኖም አብሮ አንድ ጉድ ተነገረኝ። በደሜ ውስጥ የኤች ኤቪ ቫይረስ መኖሩን።

መርዶው ሲነገረኝ ዙርያ ገባው ጨለማ ሆነብኝ። መሬት ተከፍታ ብትውጠኝም ወደድኩ ስትል ታሪኳን ያጫወተችን የዛሬ እንግዳችን ገነት መላኩ ናት። (ስሟ የተቀየረ)

በራሷ አንደበት ታሪኳን ያወጋችን ገነት ኤች አይቪ አለብሽ ስትባል በፍፁም ዕውነታውን ልትቀበል አልቻለችም። ምክንያቱም ባለቤቷ ሹፌር ቢሆንም መስክ የሚያስወጣ ሥራ የለውም። በቤተሰቡ ላይ ማግጦ እንዲህ ዓይነት ችግር ያመጣልም ተብሎ የሚታማ ሰው አልነበረም። ሆኖም ለብዙ ጊዜ እንዴት መጣና ማን አመጣው እየተባባልን ተፋጥጠን ቆይተናል ትላለች።

አንዳችን አንዳችንን ብንጠረጥርምና ሺህ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ብንወያይም ቫይረሱ በማናችን ሳቢያ እንደመጣ ማወቅ አልቻልንም። ቆይቶ የሰፈር ልጆች ተሰባስበን የምናግዘው አንድ ወጣት እንደነበረ ትዝ አለኝ። ነፍሱን ይማረውና ወጣቱ ለእናቱ አንድ ነው። በተኛበት አልጋ ላይ የምናደርግለት እንክብካቤና ድጋፍ ይሄን ሰብአዊነት ታሳቢ ያደረገ ነው። ሆኖም በፍፁም የደም ንክኪ እንዳልነበረን እርግጠኛ በመሆኔ ወጣቱን መጠራጠሬን አቆምኩ።

ሆኖም ሁኔታውን መቀበል ስላልቻልኩ መሬት ላይ



**የኤች አይቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ጽንስ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የፀረ የኤች አይቪ መድሃኒት በአግባቡ መውሰድም ያስፈልጋል**

ተንበርክኬ ፀጉሬን እየነጨሁ አለቅሳለሁ፤ የአርባ ቀን ዕድሌን በፀጋ መቀበል አቅቶኝ ሌሊት ሁሉ አሸዋ ላይ ተንበርክኬ ሳነባው ኖሬያለሁ። በእጅጉም በሕይወት በመኖሬ ተስፋ ቆርጫለሁ።

የካዛንቺስ ጤና ጣቢያ የምክር አገልግሎት ባለሙያዎች በቀላሉ ሊያረጋጉኝ ባይችሉም በሪፈር ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ልከውኝ ነበር። ሆስፒታሉ በፊናው ንጋት በተሰኘና አሁን የት እንዳለ የማላውቀው ፕሮጀክት ውስጥ እንድታቀፍ አደረገኝ። ይሄኔ ሲዲ ፎሬ 900 በመሆኑ መድሃኒት አላስጀመሩኝም። ፈጥኖ መድሃት የሚጀምረው ሲዲ ፎሩ ከ500 በታች የሆነ ነው። ለነገሩ የባለቤቴ የሲዲ ፎር መጠን እዚህ መካከል በመሆኑ መድሃኒት የጀመረው ቀድሞኝ ነው። ቆየት ብዬም እኔ ሲዲ ፎሬ 900 ቢሆንም በማርገዜ ምክንያት መድሃኒት ተጀመረልኝ። በንጋት ፕሮጀክት አማካኝነት እኔን ጨምሮ 50 ቫይረሱ በደማችን ያለብን እናቶች ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሰባተኛ ፎቅ ላይ ልጆቻችንን ወለድን።

በየጊዜው አንድ ፌስታል ሙሉ ኪኒን ተሸክሞ መግባት ይሰለቻል። በየቀኑ እስከ 10 ፍሬ የሚደርሰውን መድሃኒት መቃሙም መፈጠርን ያስጠላል። በእርግዝና ሰዓት ዋናውን የፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት ስወስድ ቆይቻለሁ። ልጄን በሰላም ተገላገልኩ፡፤ሆኖም ልጄም እንደኔው በደሟ ውስጥ ቫይረሱ መኖሩ ተነገረኝ። አምርሬ አለቀስኩ፤ከእኔ አልፎ ልጄን ለመከራ መዳረጌ እራሴን እንድጠላ አደረገኝ።

አሁን የሚያሳስበኝ የልጄ ጤንነት ነው። ቫይረሱ እንዳይጎዳብኝም ጥንቃቄ አደርግ ነበር። ከተወለደች በኋላ ጡት እያጠባኋት የምወስደውም መድሃኒት ነበር ። ልጄን እስከ ስድስት ወር የእናት ጡት ብቻ እንጂ ሌላ ምንም የምትወስደው አልነበረም።

ሆኖም ጎን ለጎን በፈሳሽ መልክ የምትወስደው መድኃኒት ከባድ ነበር። ልጄ በፈሳሽ መልክ የምትወስደው መድሃኒት በራሱ ራሱን የቻለ ራስ ምታት ሆኖብኝ ቆይቷል። መድሃኒቱን ከወሰደች በኋላ ከ30 ደቂቃ በፊት ካስመለሳት የግድ ተደግሞ ይሰጣታል። በዚህ ምክንያት በምትሰቃይበት ሁኔታ በየጊዜው ለፈጣሪዬ አለቅስ ነበር። ይሄ ዘመን ለኔ ፍፁም ብርሃን የማይታይበት ጨለማ ነበር። የጨለማ ዘመን የምልበት ብዙ አሁን ከደረስንበት ጋር የሚነፃፀሩ ምክንያቶች አሉኝ። እኔ ነፍሰ ጡር ስለሆንኩ መድሃኒቱን እንድወስድ ይፈቀድልኝ እንጂ ብዙ ህሙማኖች የመድሃኒት እጥረት ስለነበር የፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት ሳንወስድ በሲዲፎራችን መጠን ተገድበን ለረጅም ዓመት ለመቆየት እንገደድ ነበር።

ዛሬ ግን ማንኛውም ቫይረሱ በደሙ ያለበት ሰው ፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት ይወስዳል። ራስን ግልጽ አድርጎ ቫይረሱ በደም ውስጥ መኖሩን መናገር ይቅርና በመድሃኒት አወሳሰድና በአንዳንድ ሁኔታዎች በግል ተነሳሽነት ሐኪሞች ከሚያደርጉት ያለፈ የምክር አገልግሎት አልነበረም። አሁን ግን የምክር አገልግሎቱ ከእንክብካቤ ጋር በስፋት ይሰጣል።

ለማንኛውም ወደ ራሴ ልመለስና የትኛውንም ሐኪሞች ከመድሃኒት ጋር ተያይዞ የሚመክሩኝን ምክር ሳልተገብር ቀርቼ አላውቅም። ከራሴ አልፌ ተርፌ ልጄ ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ኖሮ እንድትወለድ ምክንያት በመሆኔ ተስፋ ብቆርጥም በኔም ሆነ በልጄ ጉዳይ ከመድሃኒት አወሳሰድ እስከ ሰዓቱና ምጣኔው የመከሩኝን ዝንፍ ሳልል ነው የምፈፅመው።

ማጥባት ያቆምኩት ልጄን በወለድኩ በዘጠነኛው ወር ነው። ከአንድ ወር በኋላም መድሃኒቱም ቆመ። በእርግዝና ሰዓት ዋናውን የፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት ስወስድ ቆይቻለሁ። ከተወለደች በኋላ ጡት እያጠባኋት የምወስደውም መድሃኒት ነበር ። ሆኖም ጎን ለጎን በፈሳሽ መልክ የምትወስደው መድኃኒት ከባድ ነበር። በዘጠነኛ ወሩ ጡት ሳቆም አቁሜ ከአንድ ወር በኋላ መድሃኒቱ አብሮ ቆመ። ይሄኔ የመጀመርያ ምርመራ ተደረገና ልጄ ከቫይረሱ ነፃ ተባለች። ለመጀመርያ ጊዜ ከውስጠ ተደሰትኩ፤አምላኬንም አመሰገንኩ።

ከዓመት ከስድስት ወር ቆይታ በኋላ « ግራጅዌሽን» የተሰኘውን ምርመራ ተመረመረች። በምርመራው አሁንም ከቫይረሱ ነፃ መሆኗ ተረጋገጠ። የጨለማው ዘመን አልፎ የብርሃን ዘመን መጣ። እንዲህ ከሆነ ለምን ሁለተኛ ልጅ አልወልድም አልኩ። አሁን ገና ከጽንሱ ከእናት ወደ ልጅ ቫይረሱ እንዳይተላለፍ የሚያደርገውን ሕክምና ተከታትየ ሁለተኛ ልጄን ወለድኩ።

መቆየት ደግ ነው። የመጀመርያ ልጄ ዘንድሮ 19ናኛ አመቷን ይዛለች። ለ12 ኛ ክፍል ማትሪክ ፈተና እየተዘጋጀች ነው። ሁለተኛ ልጄ ደግሞ ዘንድሮ ሰባተኛ ዓመቷን ደፍናለች። ሆኖም ልጆቼ እስካሁን በደሜ ውስጥ ኤችአይቪ እንዳለ አያውቁም። ልጄ ማትሪክ እንደተፈተነች ታሪኬን በሙሉ ለመንገር ወስኛለሁ። አበቃሁ።

# ዓለም አቀፍ

## ፕሬዝዳንት ባይደን ባለጸጎች ላይ ከፍተኛ ግብር የሚጥል ሕግ አጸኑ

ጆ ባይደን በአየር ንብረትና በጤና ዙርያ የቀረቡ ረቂቅ ሕጎች ላይ ፊርማቸውን አኖሩ። የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን በፊርማቸው ያጸኑት ሕግ በሃብታሞች ላይ ጠንከር ያለ ግብር የሚጥል ነው። ይህ ረቂቅ ሕግ ከፍተኛ ገቢ ባላቸው ኩባንያዎች ላይ ግብር በመጣል በአየር ንብረት ለውጥና በጤና ዙርያ ለሚሠሩ ሥራዎች የሚውል ገንዘብ የሚያስገኝ እንዲሆን የተዘጋጀ ነው።

ባይደን ትናንት በረቂቅ ሕጉ ላይ ፊርማቸውን በማኖር ሕግ እንዲሆን አጽንተውታል። ይህ ሕግ ከዚህ ወዲያ በጤና ዙርያ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች ዋጋ እንዲስተካከል የሚያደርግ ነው። የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ለዓመታት በሚታዘዙ መድኃኒቶች ዋጋ ላይ ቅናሽ እንዲደረግ ሲወተውቱ የቆዩትን ጥያቄ ይመልሳልም ተብሏል።

ዲሞክራቶች በዚህ ረገድ የሦስት ትሪሊዮን ዶላር ጥቅል ዕቅድ የነበራቸው ሲሆን ይህ አሁን በፕሬዝዳንቱ የተፈረመው ሕግ ግን ከዚህ የገንዘብ መጠን በእጅጉ ያነሰ ነው። ይህ ሕግ ጆ ባይደን ወደ ሥልጣን ሲመጡ አደርጋቸዋለሁ ብለው ለደጋፊዎቻቸው ቃል ከገቧቸው ጉዳዮች አንዱና ዋንኛው ነበር።

ጆ ባይደን ይህን ረቂቅ ሕግ ማድረጋቸው ምናልባት በቅርብ ለሚካሄደው የአሜሪካ የአጋማሽ ምርጫ (ሚድተርም ኢሌክሽን) በመራጮች ላይ ተጽእኖ እንዲኖረው የታሰበ ነው የሚሉ አልጠፉም። የአጋማሽ ዘመን ምርጫ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሥልጣን በያዘ በሁለተኛ ዓመት የሚደረግ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት የማሟያ ምርጫ ነው። ይህ ምርጫ በመጪው ኅዳር ይደረጋል።

የአጋማሽ ዘመን ምርጫው በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የዲሞክራቶች የበላይነት እንዲያበቃ ሊያደርግ ይችላል የሚል ግምት አለ። ይህ ፕሬዝዳንቱ ትናንት ማክሰኞ ሕግ ያደረጉት ረቂቅ በውስጡ የአየር ንብረትና የጤና ዘርፎችን የያዘ ነው። መጠኑም በድምሩ 700 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን የአየር ንብረት ለውጥን ለመታገል እና ለጤና ጥበቃ የሚውል ነው።

ከዚህ ገንዘብ ውስጥ 375 ቢሊዮን ዶላሩ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚውል መሆኑ በአሜሪካ ታሪክ ለዚህ ዘርፍ ከፍተኛ በጀት ተደርጎ ተወስዷል። የአየር ንብረት ሳይንቲስቶች ይህ ገንዘብ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ሊያደርግ ቢችልም ለውጡ ግን መጠነኛ ነው ብለዋል።

በዚህ ሕግ መሠረት አሜሪካ በተለያዩ መንገዶች ወደ ከባቢ የምትለቀው የበካይ ልቀት በፈረንጆቹ 2030 በ44 ከመቶ ዝቅ እንዲል ያስችላል። ይህ ሕግ ግዙፍ ኩባንያዎች ወደ ከባቢ የሚለቁት በካይ ጋዝን እንዲቀንሱ የሚያስገድድ ባይሆንም ወደ ታዳሽ ኃይል ፊታቸውን ካዞሩ ግን የግብር እፎይታን ይሰጣቸዋል።

የኤሌክትሪክ መኪና የሚገዙ ሰዎች ብድርን ጨምሮ ቅናሽ እንዲሁም በተራዘመ ጊዜ ክፍያ እንዲፈጽሙ ያበረታታል። በቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ምርት ላይ ኃይል ቆጣቢ ምርቶችን ለሚያቀርቡም ኩባንያዎችም ልዩ ማበረታቻን ያደርጋል።

ይህ ሕግ ከአየር ንብረት ለውጥ ሌላ በጤናው ዘርፍ አዲስ ቅናሽን ይዞ መጥቷል። በተለይም እድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ ለሆኑ አሜሪካዊያን የታዘዙላቸውን መድኃኒቶች በቅናሽ እንዲያገኙ በጤና መድኅን በኩል መንግሥት ከመድኃኒት አቅራቢዎች ጋር እንዲደራደር ያስችለዋል።

ባይደን ይህን ረቂቅ ሲፈርሙ “ይህ ለአሜሪካ ታሪካዊ ቀን ነው” ያሉ ሲሆን ይህ ረቂቅ ሕግ እንዳይሆን እያንዳንዱ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት



የሪፐሊካን አባል ተቃውሞት ነበር ብለዋል። ይህ ሕግ በግዙፍ ኮርፖሬሽኖች ላይ ዝቅተኛው የግብር ወለል 15 በመቶ እንዲሆን ያዛል። ዓመታዊ ገቢያቸው ከ400ሺህ ዶላር በታች ለሆኑ ዜጎች የግብር ጭማሪን እንደማያስከትል ተነግሯል።

ይህ ሕግ የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት በርካታ ተጨማሪ የግብር ወኪሎችን እንዲቀጥር የሚያስችለውን 46 ቢሊዮን ዶላር ያቀረበ ነው። ይህ ሕግ ተፈጻሚነቱ በሁለት ዓመት ሊዘገይ ይችላል። ረቂቁ ሕግ ለመሆን በተቃረበበት ጊዜም በርካታ በአሜሪካዊያን ሕይወት ላይ ለውጥ ያመጣሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው አንቀጾች እንዲወጡ ተደርገዋል።

ከእነዚህ መሀል የስኳር በሽተኞች ኢንሱሊን ለመግዛት በሚያወጡት ዋጋ ላይ የዋጋ ምጣኔ ያስቀምጥ የነበረው አንቀጽ ይገኝበታል። ትሬቨር ሚልተን የ21 ዓመት ወጣት ነው። ይህ ረቂቅ ባለቀ ሰዓት እንዲወጡ በተደረጉ አንቀጾች ምክንያት ቅሬታን ፈጥሮበታል። ከ12 ዓመቱ ጀምሮ የስኳር በሽተኛ የሆነው ትሬቨር በወር ለኢንሱሊን ብቻ 210 ዶላር ይከፍላል። “ሁልጊዜም ሕይወቴን ለማቆየት 210 ዶላር መክፈል እንዳለብኝ ሳስብ እደነቃለሁ” ይላል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፦ www.press.et
ፌስቡክ፦ Ethiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ሐሙስ ስፖርት



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት
ነው!

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን በሴካፋ እያንፀባረቀ ነው

**ብርሃን ፈይሳ**

በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ የክለቦች ቻምፒዮና ተሳታፊ በመሆን ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ፤ የምድብ ሁለተኛ ጨዋታውን ዛሬ ከብሩንዲው ፎፊላ ፒኤፍ ጋር ያደርጋል። ከጠንካራ ቡድኖች መካከል አንዱ የሆነው የንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን ጨዋታውን በአሸናፊነት እንደሚያጠናቅቅም ይጠበቃል።

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ካለፈው ዓመት አንስቶ እንዲጀመሩ ካደረጋቸው ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ቻምፒዮና ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ እየተካሄደ ሲሆን፤ ዛሬ የምድብ አንድ ሁለተኛ ጨዋታዎች ይካሄዳሉ። በዚህም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ ከብሩንዲ አቻው ፎፊላ ፒኤፍ ጋር ይጫወታል። የምድቡ ሌላኛው ጨዋታ ደግሞ በሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ እና የዛንዚባር ዋሪየርስ ኲዊንስ ክለቦች መካከል ይካሄዳል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ክለብ አምና በኬንያ አስተናጋጅነት በተደረገው ቻምፒዮና ላይ ዋንጫ ለማንሳት ቢቃረብም ስላልተሳካለት በሁለተኛነት ማጠናቀቁ የሚታወስ ነው። ይሁን እንጂ ንግድ ባንክ የዚህ ዓመት የቀጣናው አሸናፊ በመሆን ወደ አህጉራዊው ቻምፒዮና ለማለፍ ራሱን አጠናክሮ ወደ ውድድሩ ገብቷል። ለዚህም ስድስት ተጫዋቾችን ከሀገር ውስጥ ክለቦች ማስፈረሙ የሚታወስ ነው። ክለቡ ከነሀሴ 7 እስከ 22 ቀን 2014 ዓም በሚካሄድው ቻምፒዮና ላይ ውጤታማ ለመሆን አራያት አዶንግ፣ ኒቦኚ የን፣ ቅድስት ዘለቀ፣ መሳይ ተመስገን፣ ብርቄ አማረ እና ናርዶስ ጌትነትን ማስፈረሙ ይታወቃል። ጠንካራ የሴት እግር ኳስ ቡድኖች እምብዛም



የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን በዛሬው ጨዋታ ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቶታል፣

በሌለበት በዚህ ቃጠና ንግድ ባንክ ካለው ልምድና ጠንካራ ተጫዋቾች አንጻር የዛሬውን ጨዋታ እንዲሁም ውድድሩን በአሸናፊነት እንደሚያጠናቅቅም ይገመታል።

ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ የሚደረገው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና በታንዛኒያዋ ከተማ አሩሻ አስተናጋጅነት እየተካሄደ ቀናትን አስቆጥሯል።

በውድድሩ ላይ ስምንት ቡድኖች ተካፋይ ሲሆኑ፤ በሁለት ምድብ ተከፍለውም የዋንጫ ፍልሚያቸውን ያደርጋሉ። በዚህም መሰረት በመጀመሪያው ምድብ የኢትዮጵያውን ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ ጨምሮ፤ የዛንዚባሩ ዋሪየርስ ኲዊንስ፣ የብሩንዲው ፎፊላ ፒኤፍ እና የሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ ተደልድለዋል።

በሌላኛው ምድብ ደግሞ የአዘጋጇ ሃገር ታንዛኒያ ክለብ የሆነው ሲምባ ኲዊንስ፣ የጅቡቲው ጋርዴ ሪፐብሊካን፣ የዩጋንዳው ሲ ኮርፖሬት እንዲሁም የደቡብ አፍሪካው ዩ ጆይንት ስታርስ ይገኛሉ።

የምድብ ጨዋታዎቹ በሳምንቱ መጀመሪያ አንስቶ እየተካሄደ ሲሆን፤ የ2014 የኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪሚየር ሊግ አሸናፊ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ በከፍተኛ የግብ ብልጫ ድል ተቀዳጅቷል። በመጀመሪያው የምድብ ጨዋታ ከዛንዚባሩ ዋሪየርስ ኲዊንስ ጋር የተገናኘው ንግድ ባንክ 9 ለምንም በሆነ ውጤት ነበር ተጋጣሚውን የረታው። በጨዋታው ሁለት ተጫዋቾች ሃትሪክ የሰሩ ሲሆን፤ አምበሏ ሎዛ አበራ 5 ግቦችን ከመረብ ስታሳርፍ ሌላኛዋ ተጫዋች መዲና አወል ደግሞ 4 ግቦችን ከመረብ ማዋሃዳቸው የሚታወስ ነው። ይህም ተጫዋቾቹን ገና ከውድድሩ ጅማሬ አንስቶ ከፍተኛ ግብ አስቆጣሪዎች ሊያደርጋቸው ችሏል።

በቻምፒዮናው ላይ ኢትዮጵያ ከንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ቡድን ባሻገር በዓለም አቀድ ዳኞቿም እየተወከለች ትገኛለች። እነርሱም በካፍ ጥሪ መሰረት በዋና ዳኝነት ጨዋታዎችን የምትመራው ጸሃይነሽ አበበ እንዲሁም ረዳት ዳኛ ወይንሸት አበራ ናቸው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሴቶች እግር ኳስ ቡድን ኬኒያ ላይ ተዘጋጅቶ በነበረው የመጀመሪያው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና ላይ ሁለተኛ ደረጃን ሲይዝ፤ የኬንያው ቪጋ ኲዊንስ አሸናፊ ነበር። በቻምፒዮናው ላይ ኢትዮጵያዊቷ ሎዛ አበራ 13 ግቦችን በስሟ በማስቆጠር ቀዳሚ ተጫዋች እንደነበረች ይታወሳል።

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## በስኬታማ አፈፃፀም የታጀበው በጀት አመት

**ታምራት ተስፋዬ**

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀምን ገምግሟል፡፡ በዚሁ መድረክ ላይም የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሪት ሄራን ገርባ ፣በ2014 በጀት ዓመት በህግ፣ በተቋሙ መዋቅርና የአሰራር ስርዓት በመፍጠር ረገድ ሶስት አንኳር ዕቅዶችን ባለስልጣን መስሪያቤቱ አስቀምጦ ወደ ስራ መግባቱን አስታውሰው፣‹‹በአፈፃጸም በኩል ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አበረታች ስራዎች ተሰርቷል››ብለዋል።

በጀት ዓመቱ ባስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ስያሜ የሚመጥን የተቋሙን ገላጭ ምስልና ማንነት በመቅረጽ ተቋሙን በህብረተሰቡ ህሊናና ልብ ውስጥ ለማስቀረት ከስያሜና ከተልዕኮ አንስቶ የተቋሙ መለያ ብራንድ በመቀየር ወደ አዲስ ምዕራፍ የተሸጋገረበት ነው፡ ፡ከዚህ ባሻገር በመድሃኒት ተቋማት ኢንስፔክሽን የአይሶ 17020 ዕውቅና ሰርተፍኬት ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ያገኘበትም ነበር፡፡

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ኢንስቲትዩት በተካሄደው በዚሁ የግምገማ መድረክ ላይ ከዋናው መስሪያ ቤት፣በዳይሬክቶሪቶችና በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አማካኝነት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በውይይቱ ላይም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት በተለይ በህገ ወጥ የምግብና የጤና ግብዓቶች ዝውውር ቁጥጥር ረገድ አበረታች ስራዎች መሰራቱ ተገልጿል፡፡በ2014 በጀት ዓመት የኮቪድ 19 ክትባትን ጨምሮ የመድኃኒቶችን ደህንነት ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ፣የምግብ ላብራቶሪን በአዲስ መልክ በማደራጀት የተለያዩ



ምርመራዎችን እንዲጀምር ከማድረግ አኳያ፣በምግብ ምርት ላይ ቁጥጥር በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎችን ከመውሰድ አንጻር ውጤታማ ተግባራት መከናወናቸውም ተጠቁሟል፡፡

በአዲስ አበባ ደረጃ ከትንባሆ ጭስ ነጻ የማድረግ ፕሮጀክት በማስጀመር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ህብረተሰቡን በማሳተፍ እንዲሁም በሁሉም የከተማ አስተዳደር ባለቤትነት ተወስዶ መሰራት መጀመሩ በአመቱ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል በስኬትማነት የሚጠቀስ ነው፡፡

ህገወጥ በምግብና በጤና ግብዓት ምርቶች ላይ ቁጥጥር በማድረግ አጥፊዎችን በህግ ተጠያቂ ከማድረግ አኳያ የተሰራው ስራም አበረታች ሆኖ ታይቷል፡፡ ኮሙኒኬሽን ስራ፣ የተቋሙ የዲጂታላይዜሽን ስራዎች ፣የማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር የተሰሩ ስራዎች እና ሌሎች የላቀ አፈጻጸም የተገኘባቸው ስራዎች መሆናቸው በመግለጽ፤ ተሞክሮዎች ተቀምረው ሊሰፉ እንደሚገባቸው አስታውቀዋል፡፡

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማን ማጠናቀቂያ ፕሮግራም ላይ ፣በምግብ፣ በመድኃኒት፣ በሕክምና መሳሪያዎች እና በኮስሞቲክስ ዙሪያ የድዕረ ገበያ ቅኝት በመስራት የሚወሰዱ ናሙናዎችን ተከትሎ የሚገኙ ውጤቶችን፣የገበያ ጥናት በመሰራት እንዲሁም የተቀመጡ ህጎችና አሰራሮችን በመጠቀም ቁጥጥር በሚደረግባቸው እንደ ትንባሆ ባሉ ምርቶች ጭምር ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ተከታትሎ እርምጃ የመውሰድ ስራ ሲሰራ የነበረ ቢሆንም፤ የህብረተሰቡን እርካታ ለማረጋገጥ በቀጣይ በጀት ዓመትም የቅንጅት ስራውን በማጠናከር በሕገወጥ ምግብና የጤና ግብዓቶች ዝውውር ላይ የተሰማሩ አካላትንና ግለሰቦችን ወደ ሕግ አቅርቦ ማስቀጣት ላይ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራ ተገልጿል፡፡

ዋና ዳይሬክተሯ በገምገማው ማጠቃለያ ላይ በሰጡት አቅጣጫ፣ ‹‹በቀጣይ በ2015 በጀት አመት ተቋማዊ ግንባታን በማጠናከርና ስትራቴጂክ ዕቅዶች መሰረት በማድረግ ስራዎች መስራት እንደሚገባና ቁጠባን መሰረት ያደረገ ከብክነት የጸዳ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ስራዎችን በልህቀት በመስራት፣ የእርምት ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል ፣ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን በቁርጠኝነት በመታገል ወደ ልህቀት የሚደረገውን ጉዞ ለማሳካት ጠንክሮ በመስራት አርአያ የሚሆን ተቋም መገንባት አለብን››ብለዋል፡፡

እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጎልበት በምግብ፣በጤና ግብዓቶች እና ሌሎች የጤና ጉዳት በሚያደርሱ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ምርቶች ዙሪያ የሚደርጉ ቁጥጥሮችን ውጤታማ በማድረግ በህብረተሰቡ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን ቀድሞ በመከላከል ሃላፊነት መዋጣት እንደሚገባም አጽእኖት ሰጥተውታል፡፡ለሁለት ቀናት ሲካሄድ የነበረው የባለስልጣኑ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማም፣ቀጣይ የስራ አቅጣጫ በመስጠት ግምገማው በስኬት ተጠናቋል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ